፭

# በትዳር ውስጥ ያለ ግጭትና መፍትሄው

ሰው በሃጢአት ከወደቀ በኋላ ከመጀመሪያው አይነት ፍጹም ኃብቻ ፍጹም ወዳልሆነው ነገር ግን ወደ ፍጹምና ማደግ ወደሚችለው የጋብቻ አይነት ወደቀ። ይህም እግዚአብሔር መልካም ነው ብሎ በፈጠረው ነገር ሁሉ ከሰው ውድቀት የተነሳ ሰው የገባበትና ሰው ያለበት ቦታ ሁሉ ፍጹምናውን እንዲያጣ አደረገው።

ዛሬ በትዳር ውስጥ ያለው ችግር ሁሉ ትዳር የፈጠረው ሳይሆን በሰው ሃጢአት ምክንያት የተፈጠረ ነው። በዚህ ምክንያት ጌታ እስኪመጣና ከዚህ ሃጢአተኛ ሰውነት እስክንወጣ ድረስ እንዴት መኖር እንዳለብንና ይህ በሰው ሃጢአት ምክንያት የተበላሸውን ትዳርም ሆነ ሌላ ነገር እንዴት ለጌታ ክብር ተቀድሶ መኖር እንደምንችል መጽሃፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ማወቅ ፣ ማጥናትና ማድረግ ይገባል።

ትዳርን ስናስብ ባልና ሚስት ምን አንድ አደረጋቸው ብቻ ሳይሆን በመካከላቸው ያሉትን ልዩነቶች ምን እንደሆኑ ማወቅና ማስተዋል ያስፈልጋል። ብዙ ጊዜ በትዳር ውስጥ ያለው ችግር ሰዎች ስለ ትዳር ያላቸው አመለካከት የተዛባ መሆኑ ነው እንጂ ትዳር በራሱ ችግር ሆኖ አይደለም። ብዙ ሰዎች ስለ ትዳር ችግርና አስከፊ ገጽታው ሲናገሩ ይስተዋላሉ። እውነቱ ግን እኛ በትዳሩ ውስጥ የምናመጣው ችግር እንጂ ትዳሩ በእኛ ላይ የሚያመጣው ችግር የለም። ትዳር ትክክለኛን ሰው ማግኘት ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ ሰው ሆኖ መገኘትንም ይጠይቃልና።

> **«እውነቱ ግን እኛ በትዳሩ ውስጥ የምናመጣው ችግር እንጂ ትዳሩ በእኛ ላይ የሚያመጣው ችግር የለም። ትዳር ትክክለኛን ሰው ማግኘት ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ ሰው ሆኖ መገኘትንም ይጠይቃልና።»**

ሁላችን በዚህ ፍጹም ባልሆነ ስውነት ውስጥና በሃጢአት በተበላሸ አለም ውስጥ እንኖራለን። በዚህ ሁኔታ በዚህ ትውልድ መካከል በትዳር ውስጥ ጌታ ያዘጋጀውን በረከት እየበሉ ለመኖር በትዳር ውስጥ ያሉትን እውነታዎች ማወቅና መለማመድ አስፈላጊ ነው።

## በምድር ላይ ፍጹም የሆነ ጋብቻ የለም

በመጀመሪያ በየትኛውም ጋብቻ ውስጥ ፍጹም የሆነ ትዳር እንደሌለ ማወቅ ይገባናል። ይህንን ማወቃችን በቤታችን ውስጥ ለሚነሳው ማንኛውም ችግር ሃምሳ እጁን ይገለዋል። በማንኛውም ቤትና ትዳር ውስጥ በውጪ በሰው ፊት እንደ መልአክ መስለው በሚታዩት ውስጥ እንኳን አለመስማማት





አለ። ይህን በዚህ አለምና በዚህ ደካማ ሰውነት ውስጥ እስካለን ድረስ ፈጽሞ ማቆም አይቻልም።

ስለዚህ መፍትሄው እውቀትን አግኝቶ ለሚነሱት አለመስማማቶች ትክክለኛውን መልስ በመስጠት የመጣውን ጠላት በጋራ ተባብሮ ማባረር ነው እንጂ ትዳርን ከሌሎች ሰዎች ጋር በማወዳደር የራስን ቤት ማማረር መፍትሄ አያመጣም።

## በትዳር ውስጥ ያለ ግጭት ወይም አለመግባባት

በመጀመሪያ እንድናየው የምፈልገው ግጭት ወይም አለመስማማት ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው። ግጭት ወይንም አለመስማማት ማለት በመወዳደር ወይንም በመቃወም መንቀሳቀስ ማለት ነው።

> **«ግጭት የህይወት እውነታ እንጂ የኑሮ ዘይቤ አይደለም።»**

ከዚህ ትርጉም እንደምንረዳው በቤታችን ውስጥ ያለው ማንኛውም ችግር መነሻው ወይ ውድድር አልያም ተቃውሞ ነው። ራሳችንን ከትዳር ጓደኛችን ጋር ወይንም ትዳራችንን ከሌሎች ሰዎች ትዳር ጋር ማወዳደር ስንጀምር ሁልጊዜ ግጭት ይነሳል። ውድድር ያልተደረገልን ነገር ላይ ሲያተኩር ተቃውሞ ደግሞ የተደረገብን ነገር ላይ ያተኩራል።

በሁለተኛ ደረጃ ግጭት የተለመደ ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ማንሳት ያስፈልጋል። መልሱ አዎን ነው። ይህ ማለት ለመጣላት ወይንም ላለመስማማት ፈቃድ ለመስጠት ሳይሆን በዚህ ሃጢአተኛ አለምና በዚህ ደካማ ሰውነት ውስጥ እስካለን ድረስ ይህ የማይቀር ስለሆነ ነው። ግጭት የህይወት እውነታ

እንጂ የኑሮ ዘይቤ አይደለም። ታድያ ስለ ትዳራችን ችግር ቆመን ከማዘንና ከማማረር ይልቅ ይህ በሰው ሁሉ ያለ ስለሆነ የችግሩ መንስኤ ወይንም ምክንያት ምን እንደሆነ አውቆ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ትልቅ ብስለት ይሆናል።

ከዚህ በታች የሃሳብ አለመስማማት ወይም በሃሳብ አለመግባባት የተለመደ ነው ያልኩበትን ምክንያት እናያለን። በሮሜ ምእራፍ 7፥1 ላይ ሰው በሚኖርበት ዘመን ሁሉ ህግ እን ዲገዛው አታውቁምን? ይላል። በዚህ አለም ላይ ያለ ማንኛውም ነገር ሥርዓትና ህግ አለው።

ለምሳሌ ሰውም ሆነ ተሽከርካሪ በምድር ላይ ያለችግር መራመድና መሄድ የሚችሉት በስበት ህግ መሰረት ነው። መኪ ናን ያየን እንደሆን የመኪናው ጎማ በሚኖረው ስበት እያለቀ ተሽከርካሪው ያለችግር እንዲሄድ ያደርጋል። ሰው ይህንን ህግ ስለተረዳ ጎማው እንደሚያልቅ አስቀድሞ ስለሚያውቅ ላለቀው ጎማ ተለዋጭ ጎማ ያዘጋጃል እንጂ ለምን ጎማዬ አለቀ ብሎ አያጉረመርምም።

ልክ እንደዚሁ ሀግ ሁሉ ፖዘቲቭና ኔጋቲቭ፣ ብርሃንና ጨለማ ለሀይወት አውቀናቸው የምንጠቀምባቸው ሀጎች ናቸው። እነዚህን ሀጎች መለወጥ እንደማንችል ስለምናውቅ በአግባቡ እንጠቀምባቸዋለን እንጂ አይ እድሌ ብለን በሃዘን አናማርርባቸውም።

ከኔጋቲቭ ይልቅ ፖዘቲቭን ልንመርጥ እንችላለን። ይሁን እንጂ ሁለቱን በማቀናጀት የኤሌክትሪክ ብርሃንን በማግኘት እን ጠቀምበታለን። ከጨለማ ይልቅ ብርሃንን ልንመርጥ እንችላለን። ጨለማን ለመለወጥ ስለማንችል በቀን እየሰራን በጨለማ እን ተኛለን። ወይንም የኤሌክትሪክን ብርሃን በመፍጠር የጨለ ማውን ሃይል ለመቋቋም እንሞክራለን። በህይወት ውስጥ የአ





ንድ ነገር ምንነት የሚታወቀው ባለው ተቃራኒ ነገር መሆኑን በማወቅ መለወጥ የምንችለውን በመለወጥ ወይንም ያለንን ነገር በምስጋና በመቀበል እንኖራለን። ጨለማ ባይኖር የብርሃን ምን ነት አይታወቅም። ሃዘን ባይኖር የደስታን ጣስም ባላወቅን።

ለማብራራት እየሞከርኩ ያለሁት በቤታችን ያለው ችግር አይነቱ ይለያይ እንጂ በሰው ሁሉ ቤት ያለ መሆኑን በመገን ዘብና ችግራችንን የምናይበት አይታ እንጂ ችግሩ በራሱ ችግር አለመሆኑን በመገንዘብ ለህይወትም ሆነ ለቤታችን ያለን አመ ለካከት እንዲለወጥ ለመርዳት ነው።

በቤታችሁ የሃሳብ ግጭት አለ ማለት ፍቅር የለም ማለት አይደለም። ወይንም አንዱ ለአንዱ አክብሮት የለውም ማለት አይደለም። ነገር ግን ሁለት የተለያየ አመለካከት የተለያየ አስተዳደግና የተለያየ ጾታ ያላቸው ሰዎች ባንድ ቦታ መኖ ራቸው አርስ በርስ እንዲጠባበቁና እንዲደጋገፉ የሚረዳ ነው እንጂ ያለ መዋደድ ወይንም የትዳሩ መጥፎነት ምልክት አይደለም። ይልቁንም ሁላችንም የየራሳችን የሀይወት ጉድለት ስላለን አንዱ በአንዱ ፍጹም እየሆነ የሚኖርበት አለም ውስጥ ነን እንጂ ማንም ሰው ብቻውን በራሱ ፍጹምነትን ይዞ የሚኖር እንደሌለ መረዳት ይኖርብናል።

በእግዚአብሔር ቃል ላይ ሰዎች በቤተክርስትያንም ውስጥ ሆነ በግላቸው ችግር እንደገጠማቸው እናያለን። ያንን ችግር ግን እንደፈቱትና እንደውም ችግሩ ወደተሻለ ነገር እን ዳመጣቸው በግልጽ እናያለን እንጂ ችግራቸው ወደ ከፋ ችግር እንዲወስዳቸው ሲፈቅዱለት አናይም።

በፊልጵስዩስ 4፥2-3 ኤዎድያንና ሲንጢኪን የተባሉት ሁለት ሴቶች በህይወት መጽሃፍ ስማቸው የተጻፈ ከሃዋርያው ጳውሎስ ጋር አብረው በወንጌል የደከሙ ስለ ወንጌል ዋጋ የከፈሉ ናቸው። ምንም እንኳን እነዚህ ሁለት ሴቶች የዳኑ

በወንጌል ሥራ የደከሙና ስለ ወንጌል ሥራ ከሃዋርያው ጋር ዋጋ የከፈሉ ቢሆኑም በአንድ ሃሳብ መስማማት ስላልቻሉ ጠበኞች ነበሩ።

ከዚህ የምንረዳው መንፈሳዊ መሆናችን እንኳን ከችግር አያድነንም። መንፈሳዊ መሆን የሚረዳው ችግሩን ለመከልከል ሳይሆን ለመጣው ችግር ምን አይነት መልስ መስጠት እንዳለብን ለማወቅና ችግሩን የምንቋቋምበት ጸጋ የሚገኘው የት እንደሆነ ስለሚያሳውቀን ብቻ ነው።

በሦስተኛ ደረጃ የግጭት መነሻ ምክንያቱ ወይም መንስኤው ምንድን ነው? ብለን ልንጠይቅ ይገባል። ከዚህ በታች አንድ ባልና ሚስት ምን እንደሚለያያቸውና የልዩነታቸው መሰረት ምን እንደሆነ እናያለን።

1ኛ/ ባልና ሚለት ፍጹም የተለያየ ስብእና አላቸው

እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው ሲፈጥር እንደ እጅ አሻራችን የተለያየን አድርጎ ነው። እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ ስብእና (ማንነት) አለው። ከማንነታቸው ውስጥ ጎልቶ የሚታየው አንዱ የጾታ ልዩነታቸው ነው። በዚህ ምክንያት በወንድና በሴት መካከል ትልቅ የአስተሳሰብና የአመለካከት እንዲሁም የስሜት ልዩነቶች አሉ።

ከጥቂት አመታት በፊት አንድ ሴት የጋብቻ አማካሪ ለሆኑ አንድ ሰው በሬዲዮ ፕሮግራማቸው ላይ ወንዶች ለምንድን ነው የሴቶች ነገር የማይገባቸው? ለምን አይረዱንም? ስትል ጠየቀች። የጋብቻ አማካሪውም አሰብ አደረጉና ወንዶች የሴትን ነገር የማይረዱት እግዚአብሔር ሄዋንን ሲፈጥር ወንድ ከባድ እንቅልፍ ላይ ስለነበረ ነው። በማለት በቀልድ መለሱ። ይህን ያነሳሁት የወንድና የሴት የጾታ ልዩነት ግልጽና የጎላ መሆኑን ማወቅ ለትዳር አስፈላጊና ጠቃሚ ስለሆነ ነው።





በዘፍጥረት 5፥1 ላይ እግዚአብሔር ስለ ወንድና ሴት ልዩነት ሲናገር ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው በማለት በሁለቱ መካከል ያለውን የአፈጣጠር ልዩነቶች አንዱን ወንድ ሌላውን ሴት በማለት በግልጽ አስቀምጦአል። በሳይንስ መረጃ መሰረትም በወንዶችና በሴቶች አፈጣጠር አንድነቶች እንዳሉ ሁሉ የጎላ ልዩነቶችም እንዳሉ ይናገራሉ። እነዚህንም ከዚህ በታች በጥቂቱ እንያቸው።

በወንዱ ጾታና በሴት ጾታ መካከል ልዩነት የማይታይባቸው ወይንም አንድ የሆኑበት አራት ነገሮች አሉ።

ሀ. አጠቃላይ እውቀት
ለ. ፈጠራ ችሎታ
ሐ. ግንዛቤና
መ. የእንቅስቃሴ ደረጃ

በወንዱ ጾታና በሴት ጾታ መካከል ልዩነት የሚታይባቸው ወይንም አንድ ያልሆኑበት ሦስት ነገሮች አሉ።

ሀ. በሆርሞን የሚመራ ጸባያቸው
ለ. አንጎላቸውና
ሐ. የአካል ጥንካሬና ጽናታቸው

አንድ የሆኑባቸው ነገሮች ለብዙዎቻችን ግልጽ በመሆናቸው የሚለያዩበትን ነገሮች ላይ በማተኮር ሦስቱንም በየተራ እናያቸዋለን።

ሀ/ በሆርሞን የሚመራ ጸባያቸው

ሳይንስ በሆርሞን የሚመራ ጸባያቸው ላይ ወንድና ሴት ገና ከጽንስ ጀምሮ ልዩነት እንዳላቸው ያምናል። ልጆችን ስናይ

ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ ወንዱ በመኪና መጫወት ሲወድ ሴትዋ በአሻንጉሊት መጫወት ትወዳለች። የሚጫወቱበት እቃቸውን የተነጠቁ ልጆች ላይ ሙከራ ተደርጎ ወንዱ የተወሰደበትን እቃ በሃይል ሊያስመልስ ሲፈልግ ሴትዋ ግን ቆማ ታለቅስ ነበር።

ይህ በሆርሞን የሚመራ ባህሪይ የወንድንና የሴትን ፍላጎት ይለያል። ብዙ ሴቶች የፍቅር ፊልም ማየት ሲወዱ ወንዱ ደግሞ ጠብና ተኩስ ያለበትን ይወዳል። ሴቶች በአብዛኛው ስሜታዊ በሆነ ነገር ላይ ሲያተኩሩ ወንዱ አካላዊና ሃሳባዊ በሆነ ነገር ላይ ያተኩራል።

ለ/ የአንጎል ልዩነት

ወንድና ሴት የአስተሳሰብ ልዩነት አላቸው። ልክ የአካል ልዩነት እንዳለ ሁሉ የአንጎል ልዩነት በሴትና በወንድ መካከል አለ። ይህ ልዩነት በወንድና በሴት ባህሪይ መካከል ትልቅ ልዩነት ያመጣል።

የሰው አንጎል ለሁለት የተከፈለ ሲሆን የግራ አንጎል የግራ ሄሚስፌር ሲባል የቀኝ አንጎል የቀኝ ሄሚስፌር ይባላል። እነዚህን ሁለቱን ለይተን ያየን እንደሆነ የግራው አንጎል የቋንቋ ትንተናን ፣ አገላለጽን እና የሰውነት እንቅስቃሴን ሲቆጣጠር ፣ የቀኙ አንጎል ግንኙነትን የሚረዳ የፊት አገላለጽን ስሜትን የሚያነቃቃ ወይም የሚቀሰቅስ እና የድምጽን ቶን የሚወስን ነው።

እንዱ ማወቅ የሚገባን ወንድና ሴት መረጃን ወይንም ኢንፎርሜሽንን ፕሮሰስ የሚያደርጉት በተለያየ መንገድ መሆኑን ነው። ይህም በአንጎላቸው እስፕሌንየም (Splenium) መሰረት ነው። የሴቶች እስፕሌንየም ከወንዶች ጋር ሲተያይ የሴቶቹ





ትልቅ ነው። ይህ ማለት የአንጎል ሞገድ ወይም ዊቭ እንቅስቃሴ ነው።

ይህ እስፕሌንየም ከወንዶች ይልቅ የሴቶች በጣም ትልቁን ክፍል ይይዛል። ሴቶች ችግርን ለመቋቋም የቀኙንም የግራውንም አንጎል ሲጠቀሙ ወንዶች ግን አንዱን ብቻ ነው የሚጠቀሙት። በዚህ ምክንያት ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ችግርን የመቋቋምና በችግር ላይ ቶሎ መፍትሄ የማግኘት አቅም አላቸው።

ሌላው የሚገርመው ወንድና ሴት ግንኙነት (Commu- nicate) የሚያደርጉበት መንገድ የተለያየ መሆኑ ነው። ይህም በአንጎል ውስጥ ካለ ጾታን የሚለየው ክፍል ምክንያት ነው። ከዚህ የተነሳ ሴቶችን ከወንዶች ይልቅ ግንኙነት (Commu- nicate) የሚያደርጉበት መንገድ ለየት ያደርገዋል። ሴቶች በስሜታቸው ጥቃቅን ነገሮችን ሁሉ ሲያዩ ወንዱ ደግሞ አጠቃላይ ነገሮችን ያያል።

ሴቶች ግልጽ የሆነ የቃል ንግግርና ድብቅ ትርጉም አላቸው። በዚህ ምክንያት የሚሰት እሽታ እንቢታ ሊሆን ይችላል ወይንም እንቢ ማለት ደግሞ እሺ ማለት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ አንዳንዴ ወንዶች ሚስቶቻቸውን የተገላቢጦሽ መስማት ያስፈልጋቸዋል።

ሐ/ በአካል ጥንካሬና ጽናት ልዩነታቸው

ወንድና ሴት አንዱ የሚለያዩበት በአካል ጥንካሬ ነው። ይህም በጾታና በሆርሞን ላይ የተመሰረተ ነው። የወንዱም የሴቱም ክብደት አንድ አይነት ሆኖ ሴቶች 55-58 እጅ ብቻ የበላይ አካል ጥንካሬ ሲኖራቸው የወንዶች ደግሞ 80 እጅ ያህል ነው። ይህንን ለማረጋገጥ በተደረገው ጥናት አንድ

የሦስት አመት ወንድና ሴት ድንጋይ እንዲወረውሩ ተደርገው የወንዱ በርቀትም ሆነ ወደ ትክክለኛው ቦታ በመወርወር ሴትዋን በልጦአል።

እንግዲህ እነዚህ ሁሉ በወንድና በሴት መካከል ያሉ ተፈጥሮዋዊ ልዩነቶች በትዳር ላይ ትልቅ ተጽእኖ እን ደሚያመጡ ማወቅ ያስፈልጋል። የልዩነታችንን መሰረትና ምን እንድ እንደሚያደርገን ካላወቅን በስተቀር በሀይወት ላይ ለሚነሱ ማንኛቸውም አይነት ገጠመኞች የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት የማያስፈልግ ግጭትና መለያየትን እናመጣለን።

ለዚህ ነው ብዙ የጋብቻ ትምህርቶችና ሴሚናሮች መሰጠቱ አስፈላጊ የሚሆነው። መጽሃፍ ቅዱስ ህዝቤ እውቀትን ከማጣት የተነሳ ጠፍቶአል ሲል ቤተሰብንም ያጠፋ ነገር አንዱ እውቀት ማጣትና ቸልተኝነት እንደሆነ ልናስተውል ይገባል። ቤተክርስትያንም ይህንን ከግንዛቤ ውስጥ በመከተት የተለያዩ ጠንካራ ትምህርተቶችን መስጠት ብትችል ብዙ ቤተሰብን ከመፍረስ ማዳን ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔር መንግስት የሚ ጠቅሙ ቤተሰቦችን ማፍራት ትችላለች። ከላይ ያቀረብኩትን የወንድና የሴት ልዩነቶችንና አንድነቶችን መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች የምዘረዝራቸው በትክክለኛ ግንዛቤ ትክክለኛ ኑሮ እንድንኖር ይረዱናል።

## 1. ባልና ሚስት ፍጹም የተለያየ ስብእና አላቸው

በቤታችን ውስጥ ችግር እንዲነሳ የምናደርገው ባል ሚስ ትን ሚስት ደግሞ ባልዋን ያልሆኑትን በተፈጥሮአቸው ሊሆኑ የማይችሉትን ነገር እንዲሆኑ ለማስገደድ በምንሞክርበት ጊዜ ነው። ይህ የትዳር ጓደኞችንን የሚያስጨንቅ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር የፈጠረውን አፈጣጠር መቃወም ነው።





የሰውን ማንነት ወይም እግዚአብሔር በራሱ ጥበብና እውቀት ወስኖ የፈጠረውን መለወጥ አይቻልም። መለወጥ ካልቻልን ደግሞ ማድረግ የምንችለው እንዳለ መቀበል ነው። እያንዳንዱ ማንነት ለትዳሩም ሆነ ለእግዚአብሔር መንግስት ጠቃሚና አስፈላጊ ነውና።

## 2. የተለያየ የሚጋጭ አመለካከትና እምነት አላቸው

እያንዳንዱ ሰው የተለያየ አመለካከትና አይታ አለው። ይህ አመለካከትና አይታ ደግሞ የሚዳብረው በአምስቱ የስሜት ህዋሳቶቻችን ከልጅነት ጀምሮ በሰበሰብናቸው መረጃዎች ላይ የተመሰረተ ነው። ይህም ከአደግንበት ቤተሰብና አካባቢ ፣ ከተማርንበት ትምህርት ቤት ፣ ካነበብናቸው መጽሐፎች ፣ ካየ ናቸው ፊልሞችና በህይወታችን ላይ በተለያየ መልኩ ተጽእኖ ያሳደሩብን የሀይወት ችግር ወይንም ድሎች አልፎም የከሰረትና የሰኬት ገጠመኞች ጋር የተያያዘ ነው።

እነዚሀ ነገሮች ሁሉ ከልጅነት እስከ እውቀት ድረሰ በሂደት በአእምሮአችን ውስጥ ተቀምጠው ሳናውቃቸው ልማድ ወይንም ባህሪይ ይሆናሉ። ታድያ ከላይ ያየናቸው ነገሮች ሁሉ አብረውን የተወለዱ የጌታ ተፈጥሮዋዊ ስጦታዎች ሳይሆኑ ከተወለድን በኋላ ከአካባቢና ከሀብረተሰብ የተማርናቸው ናቸው።

ብዙ ጊዜ ሰዎች ከአካባቢና ከሁብረተሰብ የተማሩትን ነገሮችና የተፈጥሮዋዊውን ነገር መለየት ስለሚቸገሩ ለየትኛው ምን አይነት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው ማወቅ ሲሳናቸው ይታያሉ። ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ተፈጥሮዋዊ ስጦታ ከሆነ ልንለውጠው የማንችለው ተምረን ያገኘነው ሳይሆን አብሮን የተወለደ ነው።

ለምሳሌ የፊታችን ቀለም ቀይ ቢሆን ጥቁር ፣ ጾታችን ወንድ ብንሆን ወይንም ሴት ፣ አጭር ብንሆን ወይንም ረጅም ይሀ ተፈጥሮዋዊ የሆነ ማንነታችን ስለሆነ ልንቀበለውና ጌታን ልናመሰግንበት የሚገባ ነገር እንጂ ልናፍርበት ወይንም ልን ኮራበት የምንችልበት ነገር አይደለም። ዳዊት ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁ እንዳለ እያንዳንዱ ሰው የጌታ ልዩ የእጅ ስራ ነውና ራሱን ሊለውንም ሰው እንዳለ ሊቀበል ይገባል።

**«የአንድ ሰው ባህሪይ የአንድ ቀን ማኘት ሳይሆን የረጅም አመታት የተደመረ ልምምድ ነው።»**

እንግዲህ የእነዚሀን ማለትም የተፈጥሮዋዊውንና የባህሪይን ልዩነ ቶች ካወቅን በትዳራችን ውስጥ ለእነዚህ ለእያንዳንዳቸው የተለያየ ምላሽ መስጠት ይኖርብናል። በት ዳር ጓደኞችን ላይ ላለው ተፈ ጥሮዋዊ ለሆነው ነገር ሁሉ ልንለውጠው ስለማንችል ከመታገል ይልቅ ልንቀበለው ይገባል። ልንለውጠው ብንፈልግ እንኳን ጌታ የሰራውንና የሰውየውን ማንነት ስለምንጨፈልቅ ትዳሩንም ሆነ ያንን ሰው ከሚገባ በላይ እንጎዳለን።

የቤታችን ችግር ባሀሪይ ከሆነ ግን በተለይ ክፉ ባህሪያትን ሁሉ ልንለውጥ ይገባናል። የአንድ ሰው ባሀሪይ የአንድ ቀን ማኘት ሳይሆን የረጅም አመታት የተደመረ ልምምድ ነው። ይህንን ካወቅን ባሀሪይን ለመለወጥ ጊዜና ብዙ ትእግስት እን ደሚጠይቅ ማወቅ ከባድ አይሆንም።

ለዚህ ጥሩ ምሳሌአችን ጌታ እየሱስ ክርስቶስ ነው። ለታላቅ ሥራ ያሰባቸውን አስራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት ሲመር ጣቸው ያልለፋ ቆዳ ፣ ያልተጣራ ዘይትና ያልነጠረ ወርቅ





ነበሩ። እነዚህን ወስዶ ለጥቅም ያዋላቸው ከላይ ያየናቸውን ሁለት ነገሮች በመለየት ነበር። ይሀም ማንነታቸውን እንዳለ በመቀበልና ባሀሪያቸውን ደግሞ በመለወጥ ነበር።

የአንድ ሰውን ባሀሪይ ለመለወጥ ቢያንስ ሦስት መሰረታዊ ነገሮች ያስፈልጋሉ። አንደኛ ያልተቆጠበ ፍቅር መስጠት ፣ ሁለተኛ መልካም ምሳሌ መሆንና ሦስተኛ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲያመጣ ማስተማር ናቸው።

በመጀመሪያ እንዲለወጥ ለምንፈልገው ሰው ያልተቆጠበ ፍቅር መስጠት ያስፈልጋል። እንደምንወደው የማያውቅን ሰው ልንገስጸው ወይንም ልንመክረው አንችልም። የምንመክረው ወይ ንም የምንገስጸው ከፍቅር እንደሆነ ካወቀ ለምክሩም ሆነ ለግሳጼው የተዘጋጀ ልብ ይኖረዋል።

የነጎድጓድ ልጆች ተብለው ይጠሩ የነበሩት የጌታ ደቀመዛሙርት ያእቆብና ዮሃንስ ጌታ ሲያገኛቸው ቁጡና የበቀል ሰዎች ነበሩ። ከፈራጅነታቸው የተነሳ ጌታን እሳት ከሰማይ አውርዶ እንዲፈርድ ሲመክሩ ነበር። ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎች በጌታ አስደናቂ ፍቅር ውስጥ ስለነበሩ እየተማሩ እየተገሰጹ ህይወታቸው ተለውጦ እናያለን። ከሁሉም በላይ ዮሃንስ የፍቅር ሃዋርያ በመባል ስለ ፍቅር አስደናቂ መልእ ክቶችን ጽፎልናል።

በሁለተኛ ደረጃ ይሀን ሰው በፍቅር የገለጽንለት እውነት እውነት ይሁን እንጂ ለመለወጥ ጊዜና የሚሄድበትን መንገድ የሚያሳየው ሰው ይፈልጋል። በዚህ ምክንያት ያልተቆጠበ የህይወት ምሳሌነት ብናሳየው ከልማዱ ለመላቀቅ ተስፋና ፍላጎት ያድርበታል። የመጀመሪያውን ልማድ ከሌሎች ሰዎች ምሳሌነት እንደወሰደው ሁሉ በጊዜ ውስጥ መልካሙንም ባሀሪይ ከሚያየው ሰው ሊወስድና በእርሱ ላይ ተጽእኖ ሊመጣበት ይችላል።

በሦስተኛ ደረጃ ግን አንዳንድ ችግር በፍቅርና በምሳሌነት ብቻ የምንወጣው ስላልሆነ ያንን ሰው ስለሚያደርገው የማይገባ ባህሪይ መጥፎነትም ሆነ መውጫ መንገዱ ምን እንደሆነ እን ዲያውቅ በቂ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል። መቼም መማሪያ መንገድ ብዙ ነውና ከመጽሐፍትና ከመልእክቶች እንዲሁም የተለያየ የመማሪያ መንገድ በመፈለግ ማስተማርና እውቀት መስጠት ያስፈልጋል። እውቀት በራሱ አንድ ሃይል ነውና ያንን ሰው ካለበት ነገር ነጻ ማውጣት ይችላል።

እንግዲህ ባልና ሚስት አንዱ የአንዱን የማይገባ ባህሪይ ለመለወጥ መንገዱ ሃይለኝነት ፣ ቁጣ ፣ ንዴትና የተለያዩ ሰዎችን በትዳሩ ውስጥ ማስገባት ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት ራስን በማዋረድ ፣ በጸሎትና ከላይ ባየናቸው ሦስት መመሪያዎች መለወጥ ይቻላል።

ጌታ እየሱስ የደቀመዛሙርቱንም ሆነ የሌሎች ሰዎችን ባህሪይ ለመለወጥ እነዚህን ሦስት መሰረታዊ ነገሮችን ተጠቅ ሞአል። በፍቅሩ ፣ በምሳሌነቱና በአስተምሮቱ እንኳን በስጋ ያዩትን ዛሬም ከዘመናት በኋላ የእኛን ህይወት ለውጦበታል። እነዚህ መመሪያዎች ዘመን የማይሽራቸው የህይወት መመ ሪያዎች ናቸውና።

## 3. አለመግባባት ሲኖር (Misunderstanding)

አብዛኛውን ጊዜ አለመግባባት የሚመጣው በትክክል ሃሳብን ካለመግለጽ ነው። መግባባት (communication) ማለት አን ድ ሰው ለመግለጽ ያሰበው ሃሳብ አዳማጩ የተነገረውን ቃል ብቻ ሳይሆን ተናጋሪው የተናገረውን ቃልና መንፈስ በትክክለኛ ትርጉም ሲረዳ ማለት ነው።





ኮሚኒኬሽን ከቃል ባለፈ መልኩ በብዙ መንገድ ሊገለጽ ይችላል። ይህንንም በአጭሩ በሦስት ክፍለን ለማየት እንችላ ለን። አንደኛ በንግግር ሁለተኛ በሰውነት እንቅስቃሴ ሦስተኛ በጽሁፍ የሚገለጽ ነው። እኔ ግን በመጀመሪያ ሁለቱ ላይ ብቻ ጥቂት ልበል።

### ሀ. በቃል የሚገለጽ

በንግግር ወይም በቃል የሚገለጽ ግንኙነት ውስጥ ሁለት ዋና ነገሮች አሉ። አንደኛው የምንናገረው ቃል በውስጡ ያዘለው መልእክትና እንዴት እንደምንናገረው ወይንም የምን ናገርበት ዘይቤ ነው።

ቃል ሃይለኛ ነገር ነው። በቃል ውስጥ የሰውን ልብም ሆነ መንፈስ መስበርም መጠገንም ይቻላል። ለአንድ ሰው ራሳችንን በቃል ለመግለጽ ስንፈልግ የምንጠቀምባቸውን ቃላት መምረጥ እጅግ አስፈላጊ ነው። ለማስተላለፍ የፈለግነውን መልካም መልእክት ትክክለኛ ቃላቶችን በመጠቀም ካላስተላለፍነው ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል።

በግንኙነት አለም ውስጥ ባልና ሚስት ለትዳራቸው አስፈ ላጊና ጠቃሚ የሆነው የሚጠቀሙበትን ቃላት መምረጥ ነው። በተለይ ባለመግባባት ጊዜና በቁጣ ውስጥ ስንሆን የምንናገረው ቃል የትዳር ጓደኛችንን የምንጎዳ ከመሰለን አለመናገሩ ይመ ረጣል። የአፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም እንዲሉ አንዴ ከአፋችን ከወጣ ያ ቃል ያደረሰውን ጉዳት ለመፈወስ አመታት ሊወስድብን ይችላልና።

### ለ. በሰውነት እንቅስቃሴ የሚገለጽ

ይህ በተለይ የምንናገር ከሆነ ለምንናገረው ቃል በአእ ምሮአችን ውስጥ ምን እንዳሰብን በውስጣችን ምን እን

ደሚሰማን የሚገልጽ የሰውነት እንቅስቃሴ ነው። እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ከምንናገረው ቃል ጋር የሚያስተላልፈው መልእክት አለ። ይህም ራሳችንን ፊታችንን እጃችንን ወይም የእጃችንን ጣቶችና እግራችንን በመጠቀም የምናስተላልፈው መልእክት ነው።

ለምሳሌ ራሳችንን ስንጠቀም ራስን መነቅነቅና ማቀርቀር ፊታችንን ስንጠቀም ፊትን በማጨማደድ መኮሳተር ፣ የመሳቅ ፣ የማዘን ፣ የመገረምና የጥርጥር ፊት ማሳየት ፤ እጃችንን ስንጠቀም ደግሞ ጣትን መጠቆም ፣ ጸጉርን ማሸት ፣ አፍን ወይንም ፊትን በእጅ መንካትና እጅን ማወራጨት ፤ እግራችንን ስንጠቀም ደግሞ እግርን ማጣመር ፣ መዘርጋት ፣ ማንቀጥቀጥና መሬትን በእግራችን መዳፍ መጠፍጠፍ የመሳሰሉት ናቸው።

ይህ አይነቱ የሰውነት እንቅስቃሴ በአብዛኛው በፊታችን ፣ በእጃችን ወይንም በአጠቃላይ የሰውነት እንቅስቃሴአችን ላይ የሚገለጽ ነው። እንደነዚህ አይነት የሰውነት እንቅስቃሴአችን በሁለት ሲከፈሉ አንደኛው በፈቃዳችን ላይ የተመሰረተ ሲሆን ሁለተኛው ያለ ፈቃዳችን የሚገለጽ ነው።

ይህ ያለ ፈቃዳችን የምናደርገው የሰውነት እንቅስቃሴአችን ስንደነግጥ ፣ ስንፈራ ፣ ስናፍርና ስንገረም ነው። በፈቃዳችን ላይ የተመሰረተ የሰውነት እንቅስቃሴ የሚከሰተው ግን የምንናገረውን ሃሳብ ለማጽናት የሰዎችን ሃሳብና ፍላጎት ወይንም አትኩሮት ለመሳብና ሌሎችን ለመለወጥ ምን ያህል እኛ እንዳመንበት የምናሳይበት እንቅስቃሴ ነው።

ይህንን ማወቃችን የሚረዳን አልተናገርንም ማለት ሃሳባችንን አየገለጽን አይደለም ማለት እንዳልሆነ አንድና ሰተውል ነው። ማንኛውም የሰውነት እንትስቃሴአችን ቃል አውጥተን ባንናገር እንኳን ወይ የድጋፍ አልያም የተቃውሞ መልእክት እንዳለው መገንዘብ አለብን።





አንዳንዴ በቃል ለማስተላለፍ የፈለግነው መልእከት ለሌላው ሰው የሚጎዳ መስሎ ከታየን በሰውነታችን እንቅስቃሴዎች መልእክታችንን ማስተላለፍ እንችላለን። ይህ ግን መልእክቱ የሚተላለፍለት ሰው መልእክቱን በትክክል እንዳገኘ ማረጋገጥ ያስፈልገዋል።

## 4. ሚዛን ያልጠበቁ ነገሮች ሲኖሩ

ማንኛውንም ነገር ከሚገባ በላይ ካገነነው ችግር ይፈጥራል። በቤተሰብ ውስጥ ሊጋነኑ የሚችሉ አራት ነገሮችን ማየት ይቻላል።

ሀ. <u>የአስተዳደር ጫና</u> - ሁልጊዜ አንድን ሥራ ለአንድ ሰው ብቻ ከተውነውና የሥራ ክፍ ፍል ከሌለ ወይም ሁልጊዜ የአንድ ሰው ሃሳብ ብቻ እንዲፈጸም ሲደረግ ችግር ያመጣል።

ለ. <u>ያልተመጣጠነ አቅድ</u> - አንዱ ሊዝናና ሲወጣ ሌላውን ወደ ሥራ መላክ ወይም አንዱ አረፍት ሲወጣ ሌላው ቤት ውስጥ ልጅ ሲጠብቅ ፣ አንዱ ብዙ ገንዘብ ለራሱ ሲያወጣ ሊላው ምንም ሲያጣ ወይም ጥቂት ብቻ ሲያገኝ ችግር ያመጣል።

ሐ. <u>እምባገነንነት</u> - ወላጅ በልጁ ላይ ወይንም ባል በሚስቱ ላይ ያለውን መብት ባግባብ ካልተጠቀመ መጋጨት አይቀርም። ከአሰራ ሦስት እስከ አስራ ዘጠኝ አመት የእድሜ ደረጃ ያሉ ወጣቶች መብታቸውን ለማስጠበቅ የሚጥሩበት እድሜ ስለሆነ የወላጅ መብታችንን በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል። ለምሳሌ የጸጉር አሰራር ፣ አለባበስና በጊዜ ወደ ቤት መግባት የመሳሰሉትን ነገሮች የወላጅን መብት

መጠቀም ቢያስፈልግም ከሚገባው በላይ ከሆነ ግን ግጭት ያመጣል።

መ. <u>የተጋነነ ግምት</u> - አንድን ወጣት ልጅ የሥራን ክቡርነት ጸሎትን የመጸለይና ቤተክርስትያን የመሄድን አስፈላጊነት ለማስተማር በሌሎቹ ጊዜያቶች ትልቅ እንክብካቤ በማድረግ ልጁን ማስደሰት ያስፈልጋል። ከልጁ የምንጠብቀውን ለማግ ኘት ከእኛ የሚጠበቀውን በማድረግ ረገድ ሚዛኑን ካልጠ በቅን ቆይቶም ቢሆን ግጭት መፍጠሩ የማይቀር ነው።

## የቤተሰብ ግጭት የመፍትሄ ሃሳቦች

### ሀ. ለህይወት የምንሰጠው ዋጋ ሲመሳሰልና ሲጣጣም

በቤተሰብ ውስጥ ዋጋ የምንሰጣቸው ነገሮች ትክክል ሲሆኑ ቤተሰብ ጤነኛ ይሆናል። ከዚህ በታች ያሉት ነጥቦች በቤተሰብ መካከል ያለውን ግጭት በመጠኑም ቢሆን ሊቀንሱ ይችላሉና እንደ መፈክር አነግበን እንጠቀምባቸው።

### *አንዳችን የሌላውን ስሜት መጠበቅ*

በተቻለ መጠን ባለትዳሮች አንዱ የሌላውን ሰሜት እን ዳይጎዳ መጠበቅ ያስፈልጋል። ምንም እንኳን ከወንዶች ይልቅ የሴቶች ስሜት በቶሎ የሚጎዳ ቢሆንም ወንዶችም በጥንቃቄ ካልተያዙ ስሜታቸው በሚጎዳበት ጊዜ ለቤታቸው ያላቸው አክብሮትና ፍቅር እየተቀነሰ ስለሚመጣ በተቻለ መጠን ስሜታቸው የማይጎዳበትን መንገድ መፈለግ አስፈላጊ ነው።

### *አንዱ ሌላውን መርዳትና ማበረታታት*





ብዙ ጊዜ ሴቶች በቤት ውስጥ ጉድ ጉድ ሲሉ ወንዶች ከሚገባው በላይ ደስ እንደሚላቸው የታወቀ ነው። ይሁን እን ጂ በቤት ውስጥ የሥራ ክፍፍል ተደርጎ ሁለቱም አብረው የሚሰሩበት አይነት ልማድ ቢኖር ለቤቱ ሙቀት ይሰጠዋል። በቤት ውስጥ አብሮ መስራት የባለ ትዳሮችን ፍቅርና አንድነት ይጨምረዋል። በስራው ጊዜ መረዳዳት አንዱ ለአንዱ እቃ ማቀበል እንኳን የፍቅር ቃል ባይነገርም በራሱ ፍቅርን የመግለጫ መንገድ ነውና የራሱ ቋንቋ አለው። ከዚህም በላይ በተሰራው ስራ ላይ አንዱ የአንዱን ሥራ ማድነቅ በሥራው ላይ የማበረታቻ ቃሎች መጠቀሙ ትዳሩን ያንጸዋል።

### *ቁጣችንን ያለ ሁከት መግለጽ*

መቼም አብሮ ሲኖር ግጭት አለና የሚያስቆጡን ነገሮች መነሳታቸው አይቀርም። ይህ በራሱ ችግር አይደለም። ይሁን እንጂ ቁጣን ጥሩ ቃላትን በመምረጥ መቆጣታችንን ወይንም ማዘናችንን በትክክለኛው መንገድ መግለጽ ይቻላል። ቁጣችንን በሃይለ ቃልና በምሬት በማይገቡም ቃላቶች መግለጽ ግን ትዳሩን አጅግ ይጎዳል።

ሃኪሞች ሁለት አይነት ተቆጪዎች እንዳሉ ይናገራሉ። አንደኛቹ በአንድ ጊዜ አንድ ጥይት ብቻ እንደሚተኩስ ሽጉጥ አይነት ሲሆን ይህ በየጊዜው ለተነሳው ችግር ቁጣቸውን ወዲያው በመግለጽ የሚረሱ ሰዎች አይነት ነው።

ሁለተኛው አይነቱ ግን ልክ በአንድ ጊዜ ብዙ ጥይት መተፋት እንደሚችል ጠብመንጃ ሲሆን ይህ አይነቱ ተቆጪ ለረጅም ዘመን ሳይቆጣ ይቆይና ልክ የቁጣው ማአበል ሲነሳ አንደኛ አሁን ባስቆጣው ነገር ብቻ ሳይሆን የብዙ አመታቱን ቁጭት የሚወጣና ሁለተኛ ደግሞ ያስቆጣውን ሰው ብቻ

ሳይሆን ካሰቆጣው ነገር ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸውን በአጠገቡ ያሉትን ሰዎች ሁሉ የሚረሽን አደገኛ አቆጣጥ ነው።

ለዚህ መድሃኒቱ በቁጣችን ጊዜ እንደኛ ቢቻል ቁጣችን እስኪበርድ ድረስ አለመናገር ወይንም ምንም አለማድረግ ሲሆን ይህንን ማድረግ ያልቻለ ሰው ግን በቁጣው ጊዜ የሚናገረውን ነገር እያሰበ ለመናገር ቢሞክር መልካም ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምርም በቁጣችን ላይ ጸሃይ እንዳይገባ ወዲያው ይቅርታ መጠያየቁ የህይወት ዘመን ሥራ መሆኑን ማወቅ መልካም ነው።

### *አንዳችን የአንዳችንን ንብረት ማክበርና መጠበቅ*

ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ የኔ የሚሉት ነገር ሊኖራቸው እንደማይገባ እናውቃለን። ይሁን እንጂ ሁለቱም ደግሞ የየራሳቸው ነገር እንዳላቸው መርሳት አይገባም። ለምሳሌ ልብሰና ጫማቸው ፣ መጽሃፎቻቸው ከቤተሰብ ወይም ከሚወዱት ሰው የተሰጡ ሰጦታዎች ፣ የግድግዳ ጌጥ ፣ ወርቅ ፣ ፎቶግራፎች ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች ፣ የስራ መሳሪያዎችና በኮን ፒውተር ውስጥ ያሉ አስፈላጊ ፋይሎች የመሳሰሉት ሁሉ አንዱ የሌላውን እቃ በሚገባ አክብሮና ተጠንቅቆ መያዝ አስፈላጊ ነው። ይህ ካልሆነ ግን በትዳሩ ላይ የማይናቅ ችግር ሊፈጥር እንደሚችል ማወቅ ያስፈልጋል።

### *አንዳችን የሌላውን ለብቻ የመሆንን ጊዜ መጠበቅ*

በባለትዳሮች ህይወት ውስጥ የጋራ ጊዜ እንዳላቸው ሁሉ የግል ጊዜ ሊኖራቸው ይገባል ። ማንም ሰው ራሱን ከራሱ ጋር የሚያይበትና ከራሱ ጋር የሚጫወትበት ጊዜ ማግኘቱ ለትዳሩ ጠቀሜታ አለው እንጂ አይጎዳውም። ሰዎች ይህንን የግል ጊዜ ለተለያየ ነገር ይጠቀሙበታል። አንዳንዶች ለመጸለይ ፤ ስለ ሥራቸው ጉዳይ ለማሰብ ፤ የተለያዩ ትላልቅ ውሳኔዎችን





ለመወሰን ፤ ስለ ወደፊት ህይወት ምን እንደሚመስል ወይንም ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለማሰብ ፤ በቤተሰብ ውስጥ ችግር ሲነሳ ራስን ለማየት ወይንም የችግሩ መፍትሄ ምን እንደሆን ለማሰላሰልና ለማረፍ ይጠቀሙበታል።

ብዙ ጊዜ ይህ የግል ጊዜ በጋራ ጊዜ ስለሚዋጥ ሰው ራሱን የሚያይበት ጊዜ ሲያጣ በሌላው ላይ መነጫነጭና ስህተትን መፈለግ ይጀምራል። ይህ እንዳይሆን በተቻለ መጠን ሳይበዛ ከትዳር ጓደኛ ጋር በመመካከር የግል ጊዜው መቼና የት ለምን ያህል ጊዜ እንደሚሆን በጋራ ወስኖ ማድረጉ አስፈላጊ ነው። ይህንን ጊዜ ወስኖ መስጠት ብቻ ሳይሆን ያንን ጊዜ ማክበር ይገባል።

ይህ ጊዜ አስፈላጊ ለሆኑ የቤተሰብ ወይንም የግልና የስራ ጉዳይ ላይ ለማተኮር እንጂ ከቤተሰብ ተለይቶ ቤተሰብን የሚጎዳ ከማይገቡ ሰዎች ጋር ጊዜ የምናጠፋበት የሃጢአት መድረክ አይደለም።

### *አንዳችን ለአንዳችን ታማኝ መሆን*

ታማኝነት ለቤተሰብ ንጹህ አየር ማለት ነው። አንድ ሰው ንጹህ አየር ሲያጣ ሊታፈን እንደሚችልና ለመኖር እንደሚቸገር ታማኝ ካልሆነ ሰው ጋር መኖርም እንደዚሁ ነው። ታማኝነት ማለት በገቡት ቃል ኪዳን ላይ የተመሰረተ አንዱ ለሌላው ያለው የህይወት መስጠት ነው። ታማኝነታችንም በጊዜ በሁኔታና በቦታ የማይለወጥ ሊሆን ይገባል።

### *አብሮ መጸለይ ፣ አብሮ ማገልገልና አብሮ መኖር*

የክርስትያን ቤተሰብ ከሁሉ በላይ ዋጋ ሊሰጠው የሚገባቸው ነገሮች መካከል የመጀመሪያዎቹ አብሮ መጸለይና ጌታን አብሮ በማገልገል መኖር ነው። አብረን መጸለያችን

በጌታ ፊት ያቀረብነውን የጸሎት ርእስ እንዲሰማልን ብቻ ሳይሆን በተጋቢዎችም መካከል መተሳሰርን ፣ መከባበርንና መዋሃድን ይሰጣል። ከብዙ ውይይት ከብዙ ገንዘብና ከብዙ ክብር ይልቅ ጸሎት ይበልጣል። ገንዘብ የማይገዛውን ነገር ወደ ቤታችን የሚያመጣው አብሮ መጸለይ ነው።

በጌታ ሥራ ላይ አብረው የተጠመዱ ባልና ሚስት አደግ ታቸውም ሆነ ኑሮአቸው ተመሳሳይ ይሆናል። የማታገለግል ሚስት ባልዋ ከአገልግሎት ሲመጣ ልትረዳው አትችልም። ይህ በቤተክርስትያን ውስጥ ችግር ሲፈጥር ታይቶአል። ወንዱ ወይ ንም ሴትዋ አገልግለው አንዳቸው ሲመጡ ለሚስታቸው ችግር የሆኑ ብዙ ወንዶች ወይንም ለባላቸው ችግር የሆኑ ብዙ ሴቶች አሉ። ሁለቱም አገልጋዮች ከሆኑ ግን አንዱ ሌላውን በቀላሉ ሊረዳ ይችላል።

### ለ. ለመወያየት (ለመነጋገር) ፈቃደኛ መሆን

በትዳር ውስጥ ችግር ሲነሳ በችግሩ ላይ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ ነው። በቅድሚያ ግን ከውይይቱ በፊት ማወቅ የሚገባንን ነገሮች ማወቅ ጠቀሜታ አለው። ይህም ከሁሉ በፊት እግዚአብሔር የቤቱ ጌታና መሪ እንዲሆን ያስፈልጋል። እሱ የሰላም ንጉስ የሰላም ሁሉ ምንጭ ነውና። በሁለተኛ ደረጃ በጌታ ፊት በትክክል በመኖርና ጌታን በመፍ ራት መጸለይ አስፈላጊ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ የሰው አካሄድ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘው እንደሆነ በእርሱና በጠላቶቹ መካከል ሰላምን ያደርጋል ይላልና።

ከውይይቱ በፊት፡-

- ራስን ለማረጋጋት መሞከር
- የውይይቱ አላማ ግጭቱን ለማስወገድ እንጂ ክርክሩን ለማሸነፍ አለመሆኑን ማወቅ





- ሌላኛው ሰው ሁልጊዜ በሁሉ ነገር የመስማማት ግዴታ እንደሌለበት ማወቅ
- ችግሩንና የችግሩን መነሻ መረዳት

በውይይቱ ጊዜ ማድረግ የሚገባን፡-

- ከእርእስቱ አለመውጣት
- ከልብ በማዳመጥ ሌላኛው ሰው የሚያነሳውን ሃሳብ ማክበር
- ማለት የሚፈለገውን ነገር በግልጽ መናገር (ዙሪያ አለመዞር)
- ለሚቀርበው ነጥብ በተቻለ መጠን አጥጋቢ ምክንያት መስጠት
- የጋራ ነጥብ ላይ ትኩረት ማድረግ
- ተናጋሪው ሃሳቡን እስኪጨርስ ድረስ መጠበቅ (አለማቋረጥ)
- አንዱ ችግር ሳይፈታ ሌላ ከችግሩ ጋር የማይገናኝ ያልተፈታ ችግር አለማቅረብ
- ጥያቄ በመጠየቅ ሃሳቡን በደንብ ለመረዳት መሞከር

ከውይይቱ በኋላ ማድረግ የሚገባን፡-

- በተቻለ መጠን ችግሩን ከማውራት ይልቅ ብዙ የመፍትሄ ሃሳብ ለማምጣት መሞከር
- በአስታራቂው ሃሳብ ለመስማማት (compromise) ፈቃደኛ መሆን
- የተመረጠው የመፍትሄ ሃሳብ በትክክለኛው መንገድ እን ደተረዳችሁት ማረጋገጥ
- በውሳኔው ላይ ለመጽናት መሞከር
- ካስፈለገ ጽፎ ማስቀመጥ ጠቃሚ ነው
- ጥፋተኛ እንደሆነ ያወቀ ሰው ይቅርታ ይጠይቅ

- በጸሎት መጨረስና ከተቻለ ወጣ ብሎ አራት መብላት

ባልና ሚስት በመካከላቸው የተነሳውን ችግር ለመፍታት ከላይ የተጠቀሱትን ሃሳቦች በሙሉ በመጠቀም ሞክረው መፍትሄ ካላገኙ ለመፍትሄው አይናቸውን ወደ ሌላ መስመር መቀየር አስፈላጊ ነው። ይህም አንዳንድ ጊዜ የሚነሱት ችግሮች ከፋ ከሆኑ የመናፍስት አለም ጋር የተያያዙ ሊሆኑ ስለሚችሉ በጸምና ጸሎት የችግሩን አይነትና ስም እየጠሩ በመቃወም የሰይጣንን ሥራ ማፍረስ ይገባል። በባልና ሚስቱ ብቻ ካልተፈታም በመንፈሳዊ ነገር ወደበሰሉ ሰዎች ችግሩን በመውሰድ በጋራ ክፉውን መንፈስ መቃወም ይገባል።

አንዳንድ ችግር ከበር ሲተላለፍ የመጣ እርግማን ሊሆን ስለሚችል የችግሩን አይነት ለይቶ በማውጣት ያን አይነት ችግር በባልም ሆነ በሚስት ቤተሰብ ላይ በተመሳሳይ መልኩ በተደጋጋሚ ችግሩ መታየቱንና አለመታየቱን አጣርቶ ያንን እርግማን በተቃውሞ ጸሎት በጋራ የኢየሱስን ክቡር ስምና ደም በማወጅ ያንን የእርግማን ገመድ መበጠስ ያስፈልጋል።

ሊከሰቱ ከሚችሉት እርግማኖቹ መካከል ጥቂቶቹን መጥቀስ ቢያስፈልግ ፣ ገንዘብን አለ አግባብ መበተን ፣ ከመጠን ያለፈ ቁጣ ፣ ለድብድብ ወይም ለጠብ መነሳትና በተደጋጋሚ የሚታይ የጽንስ መጨንገፍ ወዘተ ናቸው። ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ የህክምና ክትትል የሚያስፈልጋቸው ሊሆኑ ይችላሉ ፤ ይሁን እንጂ ሃኪሞቹም ሊረዱ ካልቻሉ በጸሎት ክፉውን መንፈስ ቢቃወሙ ያንን ቤተሰብ ነጻ ማውጣት ይቻላል።



፯

# ትዳርና የቤተሰብ አመራር

እግዚአብሔር ፍጥረትን ሲያጥቅር በስልጣን ተዋረድ አንዱ በሌላው እንዲመራ አድርጎ ነው። አመራር የሌለው ፍጥረት የለም። ሁሉ በሥርዓትና በአግባብ የሚኖረው አያንዳንዱ ፍጥረት የሚመራው ክፍል ስላለው ነው።

ሥላሴን ያየን እንደሆን እግዚአብሔር አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ምንም እንኳን በሃይል ፣ በስልጣን ፣ በክብርና በእውቀት አንዱ ከአንዱ ባይበልጥም አንዱ ለአንዱ በፈቃዱ ሲገዛ እናያለን። በአለማችን ላይ ሦስት አይነት አመራር የሚገለጥባቸው ተቋሞች አሉ። እነዚህም መንግስት ፣ ቤተሰብና ቤተክርስትያን ናቸው።

የሰው ሁሉ ህይወት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ለእነዚህ አመራሮች ይገዛል። እነዚህ ሦስቱም ተቋሞች የራሳቸው የሆነ የስልጣን ገደብና የአመራር አይነት አላቸው። በዚህ መሰረት ሦስቱም ከእግዚአብሔር በተቀበሉት ስልጣን መሰረት ይመራሉ ያስተዳድራሉ።

በሮሜ 13፥1-5 ላይ ሃዋርያው ጳውሎስ ስለ ስልጣን አራት መሰረታዊ ነገሮች ያስተምራል።

1ኛ/ ስልጣን ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደሆነ፣

2ኛ/ አሁን በስልጣን ላይ ያሉት ባለስልጣኖች ሁሉ የተሾሙት በእግዚአብሔር እንደሆነ፣

3ኛ/ ስልጣንን የሚቃወም ሰው የእግዚአሔርን ሰርአት እንደሚቃወም፣

4ኛ/ ባለስልጣን የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደ ሆነ ዘር ዝሮ አስቀምጦአል። ሃሳቡን ለመረዳት አያንዳንዱን ሃሳብ በጥቂቱ ላብራራው።

## 1ኛ/ ስልጣን ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው

ባለ ስልጣንን የሚሾምም ሆነ የሚሽር እግዚአብሔር ነው። ጌታ እግዚአብሔር ያልሾመው አይሾምም እግዚአብሔር ያልሻረው ደግሞ አይሻርም። እግዚአብሔር ደግሞ የሚሾመውን ሰው የሚሾመው ቢያንስ ከሁለት ምክንያት በመነሳት ነው። አንደኛ ህዝብ ከጌታ መልካም ነገር ተገኝቶበት እንደሆነ ያ ህዝብ እንዲባረክ መልካም መሪ ይሾማል ። ሁለተኛው ግን የማይታዘዝና አመጸኛ ህዝብ ሲኖር ያንን ህዝብ ለመቅጣት ባለ ስልጣንን ይሾማል።

ስለዚህ ባለስልጣን የሚሾመው ወይ ለቅጣት አልያም ለበረከት ነው። የአለምን ታሪክ ስናይም ሆነ መጽሃፍ ቅዱሳችንን ስናጠና የተነሱትን መሪዎች ሁሉ ወይ ለቅጣት አልያም ለበረከት ተጠቅሞባቸዋል። እስከ ዛሬ ድረስ በምድር ላይ የተሾሙት መሪዎች ሁሉ ከፉ ከነበሩ ለቅጣት የተሾሙ መልካሞቹ ደግሞ ህዝብን ለመባረክ የተሾሙ ነበሩ። ማንም ራሱን ሊሾም አይችልምና።

በኢሳያስ 45፥1-7 - *«እግዚአብሔር ለቀባሁት አህዛብንም በፊቱ አስገዛ ዘንድ የነገስታትንም ወገብ አፈታ ዘንድ በሮቹም እንዳይዘጉ መዝጊያዎቹን በፊቱ አከፍት ዘንድ ቀኝ እጁን*





*ለያዝሁት ለቂ ሮስ እንዲህ ይላል። ... ስለ ባሪያዬ ስለ ያእቆብ ስለ መረጥሁት ስለ እስራኤል ብዬ በስምህ ጠርቼሃለሁ በቅልምጫ ስም ጠራሁህ አንተ ግን አላወከኝም።»* በማለት ቂሮስ የተባለ የአህዛብ ንጉስን ጌታ እንዳስነሳው እንደቀባውና እንደሚጠቀምበት ይናገራል። ይህ ንጉስ የአህዛብ መሪና ጌታን የማያውቅ ነበር። በዚህ ክፍል ላይም ራሱ ጌታ ቂሮስን አንተ ግን አላወከኝም በማለት ሁለት ጊዜ ተናግሮአል ። ይህም ሰው በጌታ የተቀባና የተሾመ ሆኖ ሳለ አምላኩን ግን የማያውቅ ነበረ። ጌታ ይህንን ሰው ያስነሳበት ምክንያት ግን ስለ እስራኤል ሲል ነበረ።

በእዝራ 1፥2 ራሱ ቂሮስ *«የሰማይ አምላክ የምድር መንግስታትን ሁሉ ሰጥቶኛል በይሁዳም ባለችው በኢየሩሳሌም ቤት እሰራለት ዘንድ አዘኛል»* በማለት የጌታን ትእዛዝ እንደ ተቀበለ ይናገራል። ከእነዚህ ሁለት ጥቅሶች የምንረዳው ቂሮስ ምንም እንኳን ጌታን የማያውቅ የአህዛብ መሪ ቢሆንም ጌታ ግን ሾመው። የተሾመበት አላማ ግን ስለ እስራኤል ሲባልና ቤተ መቅደሱን ይሰራ ዘንድ ነበረ።

እንዲሁም ንጉስ ዳዊትንም ከበግ እረኝነት ወስጄ ንጉስ አደረኩህ በማለት የሾመው ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ይናገራል። ይህም የአህዛብንም ሆነ የአይሁድ ነገስታት የተሾሙትም ሆነ የሚሾሙት ለእግዚአብሔር አላማና በእግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ያሳያል።

## 2ኛ/ አሁን በስልጣን ላይ ያሉት ባለስልጣኖች ሁሉ የተሾሙት በእግዚአብሔር ነው።

ሐዋርያው ይህንን መልእክት በሚያስተላልፍበት ጊዜ አለምን ይገዛ የነበረው የሮም ቄሳር የነበረው ኔሮ ነበር። በዚያን ዘመን ቄሳሮች ከህዝብ አምልኮንና ስግደትን ይቀበሉ ነበር። የአይሁድ ህዝብ ደግሞ ከእግዚአብሔር በቀር አምልኮና

ስግደት ለማንም አንሰጥም ስላሉ ታላቅ ስደት ተንሰቶባቸው በታላቅ መከራ ውስጥ ነበሩ።

ኔሮ እንኳን ለአይሁድ ህዝብ ይቅርና ለራሱ ህዝብ የማይራራ የራሱን ከተማ ታላቂቱዋን ሮምን እንኳን በእሳት ያቃጠለ እንደ አብድ የሚታይ መሪ ነበር። እንግዲህ ሃዋርያው አሁን ያሉት ባለስልጣኖችም የተሾሙት በእግዚአብሔር ነው ሲል ኔሮንም ጨምሮ ነው። ይህንን እውነት መዋጥ ከባድ ቢሆንም እውነቱ ግን ለእንደዚህ አይነቱም መሪ መታዘዝ የግድ መሆኑ ነው።

እሁን ያሉትም መሪዎች ሲል አላማ ነበረው። ያለፉትን መሪዎች ወይም ጌታ ሌላ መሪ ቢያስነሳ ሰዎች ለመታዘዝ ፈቃደኛ የሚሆኑ ይመስላሉ። ይሁን እንጂ መልእክቱ አሁን በአመራር ላይ ያሉ መሪዎች ሁሉ በጌታ ትእዛዝና ፈቃድ እን ደተሾሙ ማወቅና ማመን አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባል።

## 3ኛ/ ስልጣንን የሚቃወም የእግዚአሔርን ሥርአት ይቃወማል።

ሃዋርያው ባለስልጣን በእግዚአብሔር እንደሚሾም አሁን በስልጣን ላይ ያሉ ባለስልጣኖች የተሾሙት በእግዚአብሔር እን ደሆን ከተናገረ በኋላ ባለ ስልጣንን የሚቃወም ደግሞ የሚቃ ወመው የሿሚውን ስርአት ነው ይላል። ይህንን ክፍል ጠጋ ብለን ካየን ሃዋርያው እያለ ያለው ባለስልጣንን የሚቃወም እግዚአብሔርን ይቃወማል ሳይሆን የእግዚአብሔርን ሥርአት ይቃወማል ነው።

ማንም ሰው እግዚአብሔርን አግኝቶ ሊቃወመው አይ ችልም። ጌታ ታላቅና በሚደነቅ ብርሃን ውስጥ ተሰውሮ ያለ ማንም ሊደርስበት በማይችልበት ክብር ውስጥ የሚኖር አምላክ ነው። እግዚአብሔርን አግኝቶ መቃወም ፈጽሞ አይ





ቻልም። ስለዚህ ነው ሃዋርያው ሰው ባለስልጣንን ሲቃወም የሚቃወመው እግዚአብሔርን ሳይሆን እግዚአብሔር ያስቀመ ጠውን ሥርአት ነው ያለው።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሥርአት አምላክ እንደሆን በግልጽ ይናገራል። እግዚአብሔር ምድርን የሚያስተዳድርበት የራሱ የሆነ ደንብና ሥርአት አለው። ሰማያትንና ምድርን በውስጣቸው ያሉትን ነገሮች ሁሉ የሚያስተዳድረው ራሱ ባወጣው ሥርአትና ደንብ ነው። የሰማይ አእዋፋት የምድር አራዊትና የቤት እንስሳት ሁሉ እግዚአብሔር ባወጣላቸው ህግና ደንብ መሰረት ይመራሉ ይስተዳደራሉ።

በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ሰውም በዚህ ሥርአትና ህግ ውስጥ መተዳደሩ የግድ ነው። ልዩነቱ ሌሎቹ ፍጥረታት እንደ ሰው ፈቃድ የሌላቸው ስለሆኑ በተሰጣቸው ሥርአትና ደን ብ ከፍጥረት ጀምሮ እስከ ዛሬ ሲመሩ ሰው ግን በፈቃዱ እን ዲገዛ ትልቅ እድል ስለተሰጠው ይህንን ሥርአትና ደንብ በፈቃዱ በመጠበቅ ከእግዚአብሔር የተዘጋጀለትን በረከት መመገብ ይችላል።

የአንድ ነገር ውበቱ በሥርአት መሆኑ ነው። ወደ አንድ ያማረ ቤት ብንገባ ቤቱ የቱንም ያህል ባማሩ የቤት እቃዎች ያሸቆጠቆጠ ቢሆንም የቤቱ ውበት የሚታየው ግን በቤቱ ውስጥ ያሉ እቃዎች በሥርአት ቦታ ቦታቸውን ይዘው አስከተቀመጡ ድረስ ብቻ ነው። እቃ በእቃ ላይ ተደራርቦ ፣ ጠረጴዛውና ወን በሩ ተገልብጦ ፣ የወጥ ቤት እቃ ሳሎን ውስጥ ፣ የሳሎን እቃ በወጥ ቤት ውስጥ ሆኖ ብናየው ያንን ቤት ቤት ያሰኘው ነገር የተሰራበት እቃ ብቻ ሳይሆን በውስጡ ያሉት እቃዎች በቦ ታቸው በሥርአት መቀመጣቸው መሆኑን እናስተውላለን።

ሥርአት ባለበት ሁሉ ሰላም ደስታና ብልጽግና አለ። ሥርአት በሌለበት ሁሉ ደግሞ ሁከት ጠብና ድህነት አለ። ትዳርም በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ እግዚአብሔር በሰጠው በሥርአት የሚተዳደር በምድር ላይ ያለ አንድ ተቋም ነው።

እንግዲህ እግዚአብሔርን ለመቃወም ሰው ሊያደርግ የሚችለው አንድ ነገር ቢኖር እሱ ያወጣውን ሥርአት መቃወም ነው። ቤት በሥርአት ይገነባል በማስተዋልም ይጸናል። ስለዚህ የቤተሰብን ተቋም ሲመሰርት በሥርአትና በደንብ ላይ ነው። ይህም የባል ቦታና ድርሻ ፣ የሚስት ቦታና ድርሻ እን ዲሁም የልጆች ቦታና ድርሻ ምን እንደሆነ በመወሰን ነው።

ሰው ይህንን ሥርአትና ደንብ ሲጠብቅ ያን ጊዜ ቤቱ ሰላም ፣ ደስታና በረከትን ያገኛል። ዛሬ በብዙ ቤተሰብ ውስጥ ያለው የትዳር መናጋትና ትጥ ያጣ ኑሮ ምንጩ እገሩ ፣ መዋቅሩ ወይም ሌላ ነገር ሳይሆን የቤተሰቡ ሥርአት አልበኛነት ነው።

ሃዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን 5፥21-31 ድረስ ስለ ቤተሰብ አስተዳደር አራት መሰረታዊ ነገሮች ያነሳል።

ሀ. የክርስቶስ ፍርሃት (እንዳችን ለአንዳችን በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛን እንሁን)
ለ. መገዛት (ሚስት ለባልዋ ትገዛ)
ሐ. ፍቅር (ባል ሚስቱን ይውደድ)
መ. መታዘዝ (ልጆች ለወላጆች እንዲታዘዙ)።

### *ሀ. የክርስቶስ ፍርሃት (እንዳችን ለአንዳችን በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛን እንሁን)።*





ባልና ሚስት እርስ በርስ እንዳቸው ለአንዳቸው እንዲገዙ አስቀድመው ሁለቱም ለእግዚአብሔር መገዛትን ማወቅ አለ ባቸው። እንዴት መገዛት እንዳለባቸው ሃዋርያው በአንድ ትልቅ ሃሳብ አስቀምጦታል። ይህም እግዚአብሔርን በመፍራት ነው። ንጉሥ ዳዊትም በእስራኤል መንግስት ውስጥ የተሳካለት የድልና የብልጽግናን ህይወት እንዲኖር መንግስቱ የጸናለት መሪ ነበር።

ይህ እንዴት እንደሆነ ብንመረምር ግን እግዚአብሔርን በመፍራት እንደሆነ እናያለን። እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ነው። ቤት ደግሞ በጥበብ ይሰራል በማስ ተዋልም ይገነባልና ይህ እውቀት የሌለው ቤተሰብ የቤቱ መሰረትም ሆነ ጣሪና ግድግዳ የተበላሸ ነው።

እዚህ ላይ በመጀመሪያ እንዲገዙ የተጠየቁት ሁለቱም ባልም ሚስትም ናቸው። ባል ገዢ ሚስት ደግሞ ተገዢ እን ድትሆን አይደለም። ነገር ግን በእግዚአብሔር ፍርሃት አንዱ ለአንዱ እንዲገዛ ነው። ከላይ የሥላሴን አንድነት አዳየነው ወልድ ለአብ በመገዛት እንደሚኖር ባልና ሚስትም አንዱ ለአ ንዱ በመገዛት መኖር የውዴታ ግዴታቸው ይሆናል። አንዱ ለአንዱ በውዴታው ሲገዛ የእግዚአብሔርን ሥርአት በቤት ውስጥ ለመጠበቅ አያስቸግርም።

### *ለ. ሚስት ለባልዋ ትገዛ*

መገዛት የሚለው ቃል ብዙዎች ዘንድ ያለው ትርጉም የተዛባ ነው። ይህም መጨቆን ፣ መገፋትና መታሰር የሚል ነው። ሃዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን 5፥21 ላይ የተጠቀመው መገዛት የሚለው ቃል የግሪኩ ትርጉም በሥርአት ማስቀመጥ ወይንም ለአንድ ስፍራ መወከል ወይንም መካን ማለት ነው።

በዚህ ትርጉም መሰረት መግባትም ሆነ መገዛት የቦታና የሥርአት ጉዳይ እንጂ አንዱ ከአንዱ ስለበለጠ ጨቋኝ እን ዲገዛ የሚሰጥ የበላይነት ሹመት አይደለም። ምድራችን በራስ ወዳዶች ስለ ተሞላች በስልጣን ላይ የተቀመጡ ሰዎች የሥልጣንን ምንነት መልካሙን ገጽታ ገለው በክፋት እን ዲታወቅ አደረጉት እንጂ ከትናንሽ ካንፓኒዎች ጀምሮ እስከ መንግስታት አመራር ድረስ በስልጣን ተዋረድ ሲዋቀር ባለስልጣን አገልጋይ ህዝብ ደግሞ ተገልጋይ እንዲሆን ነበር።

ይህንን ለመረዳት ስልጣንን በአግባቡ የተጠቀሙ የአለማችንን መሪዎች ማየት ይበቃል። ለምሳሌ ማንዴላን ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግንና ጋንዲን። እነዚህ ሁሉ ያላቸውን የአመራር ችሎታ አንድም ሌሎችን በማነሳሳት ሲሆን ሌላውም ራስን መስዋእት በማድረግ ታላላቅ የህዝብ መሪዎች መሆናቸውን አስመስክረዋል። የሁሉም ፍልስፍና ያለ ጠብ ምሳሌ በመሆን መምራት ወይንም ለውጥ ማምጣት ይቻላል ነው።

ታላቁ መሪ ጌታ ኢየሱስም ሁሉን ለማድረግ ሙሉ ሥል ጣንና ሃይል እያለው የሰጠው የአመራር ስልት ምን እንደሆነ ሲናገር የሰው ልጅ እንዲያገለግል እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም ብሎአል። ለማምጣት የፈለገውን ለውጥ በሃይልና በግድ ሳይሆን ሊመራው ያሰበውን ህዝብ ራሱን መስዋእት በማድረግ አመራሩን በተግባር አሳይቶአል።

በአንድ መንግስት ውስጥ የወታደራዊ መዋቅር ላይ አንዱ ለአንዱ መገዛትን (መታዘዝን) ቢያቆም በአገሪቱ ላይ ታላቅ ቀውስ መነሳቱ የማይቀር ነው። አገር በሰላም ተጠብቆ የሚ ኖረው እያንዳንዱ ወታደር ከበላዩ ላለው ባለስልጣን ስለ መን ግስቱ ስልጣን ሲል ስለሚታዘዝ ነው። ጥያቄው ልክ የመሆንና





አለመሆን ሳይሆን በስልጣን ላይ ላለው የመታዘዝና ያለመታዘዝ ጉዳይ ነው።

ልክ እንደዚሁ ሁሉ ባል በሚስቱ ላይ እንዲሰለጥን ሳይሆን በቤተሰቡ ላይ አስተዳደራዊ መዋቅር እንዲኖር መጽሐፍ ቅዱስ ሚስት ለባልዋ እንድትገዛ ይናገራል። ይህ ማለት ባል ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ በእርስዋ ላይ ይሰልጥን ማለት ሳይሆን ቤቱን ለማስተዳደር ሃላፊነት የተሰጠው ለወንድ ነው ማለት ነው።

አንድ ባል ይህንን አስተዳደራዊ ስልጣን ከጌታ ሲቀበል እንዴት ማስተዳደር እንዳለበት ማወቅ አለበት። በ1ኛ ጢሞ ቴዎስ 3፥2-5 ድረስ ሃዋርያው አንድ በቤተክርስትያን ለማስተዳ ደር የሚፈልግ ሰው አስቀድሞ ቤቱን ማስተዳደር ማወቅ እን ዳለበት ይመክርና ለማስተዳደር ብቁ የሆነ ሰው ምን አይነት ባህሪያት እንደሚጠበቁበት ሲናገር ሰባት መለኪያዎችን ሰጥቶአል። እነዚህንም እንደሚከተሉት ገልጾአቸዋል።

1. የማይነቀፍ
2. ራሱን የሚገዛ
3. በስርአት የሚኖር
4. እንግዳ ተቀባይ
5. የማይሰክር
6. የማይጨቃጨቅ (የማይጣላ)
7. ገንዘብን የማይወድ

በዚህ ስፍራ ሃዋርያው የዘረዘራቸው የሥራ ብቃቶችን ሳይሆን ለሥራው የሚያበቁ ባህሪያቶችን ነው። ዛሬ በአለማ ችንም ሆነ በህዝባችን መካከል እግዚአብሔር ለማደስ የሚፈል ገው በባህሪ የተሰሩ መሪዎችን ማበጃጀት ነው።

እነዚህ መሪዎች በባህሪይ የታነጹና ቤታቸውን በሥርአት የሚያስተዳድሩ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ ሌሎች የቤተሰብ ፣ የቤተክርስትያንና የአገር መሪዎችና አስተዳዳሪዎች ይወጣሉ። ለቤተክርስትያን የሚበቁ መሪዎች የሚወለዱት ከቤተሰብ ከሆነ ለአገር የሚበቁ መሪዎች የሚነሱበትም ቦታ ቤተሰብ ነው።

ሁሉ ነገር ከቤተሰብ ይጀምራል። እያንዳንዱ ቤተሰብ ደግሞ መሪውን ይመስላል። ሚስትና ልጆቻቸውን በሥርአት የሚያስተዳድሩ ባሎች (መሪዎች) ከቤተሰብ መውጣት ከጀመሩ ከተማ ፣ ክፍለ ሃገርና አገር የመሪዎች ባለጠጋ ይሆናሉ። ይህም ለህብረተሰብ ሰላምና እድገት ታላቅ አስተዋጽኦ አለው።

በመሰረቱ ሰው የተፈጠረው እንዲገዛ (የበላይ እንዲሆን) እንጂ እንዲገዛ (የበታች እንዲሆን) አይደለም። ዘዘፍጥረት 1÷26 ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር የባህር አሶችንና የሰማይ ወፎችን እንስሳትንና ምድርን ሁሉ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ። በማለት አዳምም ሆነ ሄዋን ለመግዛት እንደተፈጠሩ ያሳያል።

ስለዚህ ሰው ለመግዛት ስለተፈጠረ ለመገዛት እንግዳ ነው። ቢታበዝ እንኳን ከእርሱ በላይ ላለው አምላኩ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው ወይንም ለተፈጠሩለት እንዲገዛ ፈጽሞ አይፈቅድም። በዘፍጥረት 3÷16 ላይ ሄዋን ሃጢአትን ከሰራች በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ፈቃድሽ ወደ ባልሽ ይሆናል ተብላ ተረገመች። ለሰው መገዛት እርግማን እንጂ በረከት አይደለም።

ጌታ እየሱስ የእኛ እርግማን የሆነው ፈቃዱን በመጣል ለአባቱ በመታዘዝ ሲገዛ ለሰው ልጅ ከወደቀበት አዘቅት መውጫውን መንገድ ማሳየቱ ነበር። ቤተክርስትያን ባሬ ለክርስቶስ የምትገዛው እርሱ አስቀድሞ ለአባቱ ስለተገዛ ብቻ





ሳይሆን ለፈጠረው ፍጥረት ለሰው ራሱን ዝቅ በማድረግ እንዲተፋበት ፣ እንዲገረፍ ፣ እንዲሰቃይና ብሎም ለመስቀል ሞት ሳይቀር ራሱን እስኪሰጥ ድረስ ስለ ተዋረደ ነው።

በዚህም ምክንያት ያለ ልክ ከፍ ከፍ ተደረገ። ምላስ ሁሉ ለእርሱ እንዲመሰክርና ጉልበት ሁሉ ለእርሱ እንዲንበረከክ ተደረገ። ልክ እንደዚሁም ሁሉ አንድ ባል ሚስቱ እንድትገዛለት መጽሃፍ ቅዱስ ቢያዝም ሴት በተፈጥሮዋ ለመግዛት እንጂ ለመገዛት ስላልተፈጠረች የቤተሰብ መሪ የሆነው ባል ለሚስቱ በመታዘዝ መታዘዝን በመገዛት መገዛትን ያስተምራታል እንጂ በስልጣን ቃል በማዘዝ እንድትታዘዝ ማድረግ ፈጽሞ አይችልም።

### *ሐ. ባል ሚስቱን ይውደድ*

የማንወደውን ሰው አንመራም የማንወደውንም ህዝብ አናገለግልም። ጌታ እየሱስ ለጴጥሮስ የቤተክርስትያንን አመራር ቁልፍ ሊሰጠው ሲል የጠየቀው ታላቅ ጥያቄ ነው። በዮሃንስ ወንጌል 21÷15-17 ላይ የዮና ልጅ ስምኦን ሆይ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? የሚል ጥያቄ ሦስት ጊዜ ጠይቆታል። ይህም አደራ የሚሰጠው ችሎታ ላለው ሰው ሳይሆን ፍቅር ላለው ሰው መሆኑን በግልጽ ያሳያል። ፍቅር ሁሉን አንድንሆን ያደርገናልና።

ጴጥሮስ ፍቅሩን በታላቅ ፍርሃትና አክብሮት ለጌታ በገለጸ ጊዜ ሦስት ጊዜም ጌታ ሥራ ነው የሰጠው። እያንዳንዱ ሥራም የበላይ ሆኖ እንዲገዛ ሳይሆን እንዲያሰማራ ፣ እንዲጠብቅና እንዲመግብ ነበር።

እውነተኛ አገዛዝ በፍቅር ይገለጻል። ይህ የአንድ ባል ትልቅ የፍቅር መግለጫ በማሰማራት በመጠበቅና በመመገብ

ላይ የተመሰረተ ነው። አንድ ቤተክርስትያን የህጻንነት ፣ የወ ጣትነትና የብስለት ጊዜ እንዳላት ሁሉ አንድም ትዳር የህጻን ነት ፣ የወጣትና የብስለት ጊዜ አለው። በእነዚህ ሦስት የእድገት ወቅቶች አንድ መሪ ለመታገስና ትዳሩንም ሆነ ቤተክርስትያንን ወደ ብስለት ለማምጣት ታላቁ መሳሪያ ፍቅር መሆኑን ማወቅ ይኖርበታል።

## 4ኛ/ ባለስልጣን የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው።

እግዚአብሔር አንድን ባለስልጣን ሲሾም ለሁለት አላማ እንደሆነ ቀደም ሲል አይተናል። በዚህ አላማ ላይ ደግሞ ሁለት ታላላቅ ስራዎች ተሰጥተውታል። መልካም የሚያደር ጉትን ለማገልገልና ክፉ የሚያደርጉትን ለመቅጣት ከእግዚ አብሔር የተሾመ ነው። በሮሜ 13፥4 ይህ የተሾመ ሰው የተሾመው ለሾመው ጌታ አገልጋይ እንዲሆን ነው። ስለዚህ አን ድን ሹም ማክበር የሾመውን ማክበር ነው። መናቅ ደግሞ ሿሚውን መናቅ ነው።

በእግዚአብሔር አይታ ባለስልጣን አገልጋይ ነው። ይሆንን ለመረዳት አንድ የትራፊክ ፖሊስን ማየት ይበቃል። ይህ በመን ግስት የተሾመ ባለስልጣን በመንገድ ላይ ያሉ መኪናዎች ሁሉ በሥርአት ያለ አደጋ እንዲንቀሳቀሱ ሥርአትን አዲያስጠብቅ በሃላፊነት የተሾመ ነው። በጸሃይም ሆነ በዝናብ በብርድም ሆነ በሙቀት ውስጥ ሆኖ በመኪና ውስጥ ያሉ ያለ ችግር እንዲሄዱ አገልግሎትን ይሰጣል።

ይህ የትራፊክ ፖሊስ ግን አንድ የመኪና አሽከርካሪ ቀይ መብራት ቢጥስ ወይንም በሥርዓት ባይነዳ ወዲያውኑ ለመቅ ጣትና አስፈላጊውን የሥልጣን እርምጃ ለመውሰድ ስይፍ የታጠቀ ነው። ስለዚህ ባለስልጣንን እንድንፈራ ወይንም እንዳን





ፈራ የሚያደርገን መንግስት ያወጣውን ህግ በመጠበቅ በመል ካም መኖር ብቻ ነው።

እንግዲህ ከዚህ ሃሳብ በመነሳት አንድ ሚስት ለባልዋ ስትታዘዝ እንደ እግዚአብሔር ቃል መሰረት የመንግስቱን ህግ ብትጠብቅ ባልዋ አገልጋይ ይሆንላታል። ነገር ግን እንቢ ብላ በመንግስቱ ህግ ላይ ብታምጽና ሥርአትን ብትተላለፍ ሥርአትን ተላልፋለችና ቤትዋ ያለ ሥርአት ወይንም የጡብ የጭቅጭቅና የስቃይ ይሆናል። ይህ ማለት ሥርአት በሌለበት ሁሉ ሥርአተ አልበኝነት እንደሚኖር ሁሉ የቤቱን ሥርአት ካፈረሱ የሥርአተ አልበኞነት ውጤትን በቤታቸው ማየታቸው የማይቀር ነው።

አንድን ቤት በሥርአት ለመምራት የቤቱን ሥርአትና የተመሰረተበትን መመሪያ መጠበቅ ነው እንጂ የአማካሪ ብዛት ፣ የውይይት ብዛትና የተለያዩ መምሪያና መመሪያ መጠቀም መልስ አይሆንም። በቅድሚያ ቤት በሥርአት ይመራልና ስርአቱ ይጠበቅ። ከዛ ስርአቱን እንዲጠበቅለት ከሚፈቅደው ጌታ ዘንድ የሰላምና የበረከትን ኑሮ መኖር ይቻላል። ለዚህ ነው ሃዋርያው በባልና ሚስት መመሪያ ላይ ብዙ ምክር መስጠት ሲችል ማስረያውን ሚስት ለባልዋ ትገዛ ባልን ደግሞ ሚስቱን ይውደድ በማለት የዘጋው።

፯

# የትዳር ማጣፈጫ ቅመሞች

ጋብቻ በትልቅ እርሻ ላይ የተተከለ አትክልት ነው። አንድ አትክልት ስለተተከለ ብቻ እንደማያድግ ነገር ግን ለማደግ የሁሉም አይነት እንክብካቤ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ትዳርም በትልቅ እርሻ ላይ የተተከለ አትክልት ስለሆነ ትልቅ እንክብካቤና ጥንቃቄ ይጠይቃል።

ማንኛውም ጤነኛ ተክል የማደግና በውስጡ ያለውን ችሎታውን ሁሉ ለማሳየት አቅም አለው። ይሁን እንጂ ገበሬው በመኮትኮት ፣ ውሃ ማጠጣት ፣ ማዳበሪያ መስጠትና በየጊዜው በላዩ ላይ የሚበቅሉትን አላስፈላጊ ተክሎች (አረሙቻ) ሁሉ እየነቀለ በማሳደግ ይንከባከበዋል። ይህንን ባያደርግ ግን አንድም ከተክሉ የሚገኘውን ሙሉ ፍሬ በጊዜው አያገኝም አልያም ተክሉ በመድረቅ ከናካቴው ሊሞት ይችላል።

ጋብቻም እንዲሁ ነው። መጋባት ብቻ በራስ በቂ አይደለም። ጋብቻ ሲጀመር በፍቅር ነው። ሁሉ ጋብቻ መኮትኮት ውሃ መጠጣትና ማዳበሪያ ማግኘት አለበት። ከዚህም በላይ በየጊዜው በትዳሩ ላይ የሚበቅሉ አላስፈላጊ ነገሮች ሁሉ በጊዜው መነቀል አለባቸው። ነገር ግን በየጊዜው እነዚህ አስፈላጊ እንክብካቤዎች ካልተደረጉለት የመድረቅ ብሎም የመሞት አዝማሚያ አለው። ታድያ ጋብቻን እንደ ማዳበሪያ ሊያፋፋት ወይንም እንዳይቀጭጭ ሊያደርጉት የሚችሉት ነገሮች ምንድን ናቸው? ጥቂቶቹን እነሳለሁ።

## 1. ምህረት ማድረግ

ሃዋርያው ጴጥሮስ *«ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት (ይቅር ልበለው) እስከ ሰባት ጊዜን አለው።» እየሱስም እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት አንዴ እስከ ሰባት ጊዜ አልልሀም አለው።* ማቴዎስ 18፥21-22 አንድ የእግዚአብሔር ሰው ይህንን ጥያቄ በማንሳት እንዲህ ብለው ተናገሩ። ለመሆኑ በቀን ውስጥ አራት መቶ ዘጠና ጊዜ ሊበድል የሚችል ሰው ማን ነው? ብዬ ሳስብ ሌላ ስላጣሁ ከሚስቴ በቀር ይህ ማንም ሊሆን አይችልም አልኩኝ አሉ።

እኝህ ሰው ደህና አስተውለዋል። ጋብቻ ያለ ምህረት አይሰራም። የጋብቻ ጣራና ግድግዳ በርና መስኮቱ የተሰራው በምህረት ነው። ምህረት ወደላይ ፣ ወደ ታችና ወደ ጎን ሰናይ ከጠዋት ጀምሮ እስከ ማታ የምንለማመደው የቤታችን ሁለመና ነው። ለአፍታ ምህረትን ከቤታችን ብናወጣ ቤቱን እናፈርሳለን።

እንዲህ ብለን እናስብ። አንድ ቤት በትላልቅ እንጨቶች ቢሰራም ቤቱ የሚቆመው እንጨቶቹን በሚያያይዙት ሚስማሮች ነው። እነዚህም ሚስማሮች ብዙ ናቸው። ሚስማሮቹ እንዱን እንጨት ከሌላው ጋር አያይዘውታል። ታድያ አንድ ሰው





በየቀኑ አንዳንድ ሚስማር ከቤቱ ላይ ቢነቅል ቀስ በቀስ ያ ቤት መፍረሱ የማይቀር ነው። ልክ እንደዚሁ ሁሉ የትዳር ማገር የተያያዘው በምህረት ሚስማር ነው። በየቀኑ አንዳንድ ሚስማር ይቅር ባለማለት ቢነቀል ቤቱ ተወላግዶ መውደቁ የማይቀር ነው።

ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ከመውጣቴ በፊት በምሰራበት ካንፓኒ ውስጥ ደንበኞች የነበሩ አንድ ባልና ሚስት አንድ ቀን ወደምስራበት ቦታ ሲመጡ አየኋቸው። ከወትሮው ለየት ባለ መልኩ ታላቅ ደስታ እየሁባቸው። ባልየው ያፏጩል ሚስትየው ከወትሮው ለየት ባለ አካሄድ ትሄዳለች። እኔም ነገሩ ግራ ስለገባኝ ሚሰትየውን ዛሬ ምን አግኝታችኋል? ለየት ያለ ደስታ አይባችኋለሁ ምን አገኛችሁ? አልኳቸው። ሴትየዋም ሳቅ አሉና ዛሬ እኔና ባሌ የጋብቻችንን ሃምሳኛውን የወርቅ ኢዩቤልዩ በአል ከልጆቻችንና ከልጅ ልጆቻችን ጋር አክብረን መመለሳችን ነው አሉኝ።

እኔም ካገባሁ ገና አንድ አመት ያልሞላኝ በመሆኔ እን ዴት ሚስትየውን ይህንን ሁሉ አመት አብራችሁ ኖራችሁ? በማለት ጠየቅኋቸው። ሚስትየውም ወዲያው ባላቸውን ዞር ብለው አዩና እኔን ዝም እንድል የሌባ ጣታቸውን አፋቸው ላይ በማድረግ እሽሽ-ሽ-ሽ-ሽ አሉኝ። እኔም ግራ በመጋባት ዝም እን ዳልኩ ባልየው የሚገፉትን እቃ ለማየት ዞር ሲሉ ሚስትየው በሁለት ቃል ብቻ እንዲህ አሉኝ። ምህረትና ትእግስት።

ከዚያን ቀን ጀምሮ ይህ ጉዳይ በልቤ ተቀረጸ። ለካ የጋብቻ መጽናት መሰረቱ ትእግስትና ምህረት ነው። ዛሬ ለምን ይሆን ይህ ሁሉ ጋብቻ እየፈረሰ ያለው? መልሱ ቀላል ነው። ምህረት ማድረግ ሲያቅተንና የትዳር ባልንጀራችን እንዲለወጥ ጊዜ ለመስጠት መታገስ ሲያቅተን ነው።

ነጮቹ ሲናገሩ ምህረት አድርግና እርሳ ይላሉ። ምህረት ማድረግ ማለት ባለፈው የተሰራውን ስህተት ጥፋትና በደል ሁሉ መርሳት ነው። መርሳት የሌለበት መማር የለም። እውነተኛ መሃሪ ሰው የተደረገበትን ይረሳል። እንደረሳን የምናውቅበት መንገድ ደግሞ ሌላ ችግርም ሆነ ያው ችግር ደግሞ ሲነሳ ባለፈው በይቅርታ የተዘጋውን ፋይል እንደገና ባለመክፈት ነው።

ይህ የእግዚአብሔር ባህሪይ ነው። እግዚአብሔር ይቅር ሲል ረስቶ ነው። ሃጢአታችሁን አላስብም። ሃጢአታችሁን ወደ ኋላ እጥላለሁ። ሃጢአታችሁን ወደ ባህር ጥዬ በዚያ እጠቀጥቃለሁ። ምስራቅ ከምእራብ እንደሚርቅ እንዲሁ ሃጢአታችሁን ከእናንተ እርቃለሁ። በማለት ዳግም ላያስታውሰው የሚያደርገውን ነገሮች ሁሉ ጽፎልናል።

ማቴዎስ 18፥21-22 እንደሚናገረው ከሆነ ይቅርታ በየቀኑ ብቻ ሳይሆን በቀን አራት መቶ ዘጠና ጊዜ ነው። ጌታ ይህንን ያለበት ምክንያት ይቅር ላለማለት ምንም በቂ ምክንያት ስለ ሌለን በየቀኑ ይቅር ለማለት ተዘጋጅታችሁ ኑሩ ማለቱ ነው። ስለ ሁሉም በደል ሁልጊዜ ይቅር ብለን መኖር የውዴታ ግዴታችን ነው።

## 2. ምርጥ ጊዜ አብሮ ማሳለፍ

እኔና ባለቤቴ ወደ ሙሉ ጊዜ አገልግሎት ውስጥ እንደገባን ሁለታችንም በአገልግሎት ውቅያኖስ ውስጥ ተጠመቅን። በቤተክርስትያኒቱ ውስጥ የነበረውን ክፍት ቦታ ሁሉ ለመሙላት ሌት ተቀን ከሰኞ እስከ ሰኞ ያለ እረፍት ማገልገል ጀመርን። ቤተክርስትያኒቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ አደገች። ብዙ ነገሮችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ተለወጡ። እኛ ግን አለቅን። ከጥቂት ወራት በኋላ ሳናውቀው በመካከላችን መራራቅ ተፈ





ጠረ። የእርስዋ ንግግር አልጥም አለኝ። እሰዋም የእኔ አልጥም አለት።

እርስ በእርስ መካሰስና መነጫነጭ ህይወታችንን እንኳን እስኪቦረቡር ድረስ ደረሰ። ያን ጊዜ ነው የነቃነው። አንድ ቀን በጸሎት ሰአቴ ጌታ ሆይ ቤትህን እንድሰራ ጠርተኸኝ ቤቴ ሲፈርስ እንዴት ዝም ትላለህ? ችግራችን ምንድን ነው? ብዬ መማጸን ጀመርኩ። ጌታም ልጄ ሆይ ችግራችሁ ምርጥ ጊዜ አብራችሁ ስለማታጠፉ ነው። ለቤቴ ጊዜ እንደሰጠህ ለሚስትህም ጊዜ ስጥ አለኝ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከባለቤቴ ጋር ትልቅ ውሳኔ ወሰንን። የነበሩንን የቅዳሜና የሰኞ በእረፍት ቀናችን የምናደርጋቸውን ፕሮግራሞች ሁሉ ዘጋን። ያንን ፕሮግራም ሰናቆም በርግጥ የምናገለግላቸው ሰዎች አዘኑብን። ይሁን እንጂ እኛ ቤታችንን አዳንን። እስከ አሁን ድረስ እንኳን ይህንን ጊዜ ለመንካት የተለያዩ ነገሮች ሲገጥሙን ቶሎ በመንቃት ወዲያው እርምጃ እንወስዳለን።

ለመሆኑ ምርጥ ጊዜ ማለት ምን ማለት ነው? ምርጥ ጊዜ ማለት ባልና ሚስት ብቻ ለብቻቸው ማንንም ሰው ወይንም ምንም ነገር ሳይጨምሩ አብረው አንዱ በአንዱ ላይ ስለለው ፍቅር ትኩረት ሰጥቶ አብረው የሚያሳልፉበት ጊዜ ማለት ነው። ይህንን ሃሳብ በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል። አንደኛው በመንፈሳዊ ነገር ላይ አብረው የሚያሳልፉት ጊዜ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ እርስ በርስ አንዱ ለአንዱ ያለውን ፍቅር የሚገልጹበት ጊዜ ነው።

የመጀመሪያው ትኩረቱ ጌታ ስለሆነ በአብዛኛው በመንፈስ አብረው እንዲፈሱና የትዳራቸው ሙጫ የሆነው ጌታ በሁለቱ መካከል ያለውን ህብረትና አንድነት መንፈሳዊ በሆነ መልኩ

የሚያያይዝበት መንገድ ነው። አንዳንዶች በየቀኑ ሌሎች አን ዳለቸው ጊዜ በሳምንት ሁለትም ሶስትም ጊዜ አብረው ይጸል ያሉ። ይብዛም ይነስ አንድ ላይ አብረው በጌታ ፊት ጊዜ ማሳለፋቸው ለትዳሩ ጤነኛ ህይወት እንዲኖረው ያደርጋል።

ሁለተኛው ግን ከዚህ ትንሽ ለየት ያለ ነው። ትዳርን ከምንከባከብበት መንገድ አንዱ አብሮ ጊዜ ማሳለፍ ነው። ይህ ሌሎች ሰዎችን ማለትም ቤተሰብን ወዳጆችን ልጆችንም እንኳን ሳይጨምር በባልና በሚስት መካከል የሚደረግ የፍቅር ጊዜ ነው።

ባልና ሚስት ቢያንስ ከተቻለ በሳምንት ሁለት ቀን ካልሆነም አንድ ቀን አብረው ቢያሳልፉ የትዳራቸውን ጤንነት ሊጠብቁ ይችላሉ። ይህን የጋራ ጊዜአቸውን በእነርሱ ላይ ብቻ ያተኮረ እንዲሆን ይገባዋል። ይህም ማለት ከሚያወሩት ወሬ ጀምሮ የሚያደርጉት ሁሉ አንዱ አንዱን የማድነቅ የማክበር የተለያዩ የፍቅርም ሆነ የአድናቆት ቃላቶችን በመጠቀም ለትዳር ባልንጀራቸው ያላቸውን ነገር የሚያፈሱበት ጊዜ ነው። የሚሉት ቃል ቢጠፋ እንኳን አብሮ መሆኑ የተለየ ስሜት ይፈጥራል።

በዚህ ምርጥ በምንለው ጊዜ ውስጥ ባልና ሚስት አብሮ መመገብ አብሮ በመናፈሻ ቦታዎች ሄዶ መዝናናት ፣ በእግር መሄድ ፣ እስፖርት መስራትና እንደየሰው ፍላጎት በሚመቻ ቸው መልኩ አብሮ ጊዜ ማጥፋቱ ትዳሩን ጤነኛ ከማድረጉም በላይ የትዳሩን እድሜ ይቀጥላል።

## 3. መከባበር

ወደ አሜሪካ እንደመጣን ወንዶቹ ለሴቶቹ ያላቸው ጥን ቃቄና አክብሮት ከማስደነቅ አልፎ ያናድደኝ ነበር። ይህም





በመኪና ውስጥ አብረው የነበሩ አቤኛሞችም ሆኑ ባልና ሚስት መኪናዋን ሲያቆሙዋት ሴቲቱ በመኪናው ውስጥ ዘና ብላ ትቀመጣለች። ወንዱ ደግሞ ከመኪናው ወርዶ ዞሮ ሴትዋ ያለችበትን የመኪና በር በመክፈት ያስወጣታል። የሚገርመኝ ወንዱ መኪናውን አቁሞ ሞተሩን አጥፍቶ ወደ እርስዋ እስኪ መጣ ድረስ ምንም አይነት እንቅስቃሴ ባለማድረግ የሴትዋ መቀመጥ ነበር።

ይህንን በማይበት ጊዜ ምን አይነት ባህል ነው? ለምንድን ነው ሴትዋን ሽባ የሚያደርጋት? አሁን በር ከፍቶ መውጣት ስራ ሆኖ ነው? ተቀምጣ የምትጠብቀው? ይህ ብቻ አይደለም ምሳ ወይንም እራት ለመብላት ወደ አንድ ምግብ ቤት ከገቡ የለበሰችውን ሹራብም ሆነ ኮት በማውለቅ ከሰቀለ በኋላ ፈጠን ብሎ በመሄድ የምትቀመጥበትን ወንበር ስቦ ያስቀምጣታል።

ምን አይነት ጉድ ነው? የመኪናውስ በር እሺ ትንሽ ከበድ ይል ይሆናል። ወንበር ስቦ መቀመጥ ምን ቁም ነገር ሆኖ ነው እሱ ስቦ እስኪያስቀምጣት የምትጠብቀው? በማለት አደንቅ ነበር። እየቆየሁ የአገሩንም ባህል እያጠናሁ ስመጣ ይህንን የሚያደርጉት ለምን እንደሆነ ገባኝ።

ወንዱ ሞኝ ሆኖ ወይንም ሴትዋ ሽባ ሆና ሳይሆን ለካ ማክበሩ ነው። ሴት በተፈጥሮ መከበርን ትፈልጋለች። ወንድ ደግሞ የበላይነትን ይፈልጋል። መጽሃፍ ቅዱስ ሴቶች ደካማ ፍጥረት ስለሆኑ ከእነርሱ ጋር በማስተዋል ኑሩ ሲል ሴት በተፈጥሮ ስስ የሆነ ቶሎ የሚጎዳ ስሜት ስላላት ነው። ለዚህ ነው የሴትን ስሜት የሚጠብቅና የሚያከብርላት ወንድ ትዳሩ ጤነኛ የሚሆነው።

ሴት በተፈጥሮ የሚያኮራትን ፣ የምትደገፈውና የምትመ ካበትን ወንድ ትፈልጋለች። ወንዱ ደግሞ ይህንን በመረዳት

የሴትዋን ፍላጎት በታላቅ እንክብካቤ ስሜትዋን ቢጠብቅላት ሴት ልክ ውሃ እንደጠገበና ጸሃይ እንዳረካው አበባ በየቀኑ የፍቅርዋን የልብዋንና ጉልበትዋን ሁሉ ያለ ገደብ ትሰጣለች።

የእኛ ባህል ለዚህ የታደለ አይደለም። ሴትን ከማክበር ይልቅ ብዙኛው በመናቅ ያምናል። ስለዚህ የብዙ ሰው ትዳር የይሁን እንጂ በርግጥ በትዳራቸው ረክተው እንዱ የሌላውን የውስጥ ፍላጎት አርክቶ ተጠጋግበው የሚኖሩበት አይደለም።

**አክብሮት ባህል ሳይሆን መጽሃፍ ቅዱሳዊ ነው።**

አክብሮት ባህል ሳይሆን መጽሃፍ ቅዱሳዊ ነው። 1ኛ ጴጥሮስ 3፥7 የቀድሞው ትርጉም ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል ኑሩ ሲል የእንግሊዘኛው ሃሳብ በአክብሮት ያዙአቸው ይላል። ሌላው ትርጉም ባሎችን ከሚስቶቻችሁ ጋር በጥንቃቄ ኑሩ ይላል። ይህም መጽሃፍ ቅዱስ ከሴቶች ጋር አብሮ ለመኖር አያያዝ እንደሚጠይቅ ማስገንዘቡ ነው።

ሃዋርያው ጴጥሮስ ከሚስቶች ጋር እንዴት መኖር እን ደሚገባ ሲናገር ሁለት መሰረታዊ ነገሮችን ጠቅሶአል። አንደኛ የሚያስፈልጋቸውን አስቦ ማድረግ ሲሆን ሁለተኛው አክብ ሮትን መስጠት ነው።

አንድ ባል የሚስቱን ልብ ማግኘት ከፈለገ በየጊዜው የሚያስፈልጋትን ነገር እስዋ ሳትነግረው እያሰበ ማድረግ አለበት። ሚስት የሚደረገው ነገር ትልቅ ወይንም ትንሽ መሆኑ ሳይሆን የምትፈልገው መታሰብዋን ነው። እስዋ በሌለችበት ስለ እስዋ አስቦ የሚያደርገው ነገር ሁሉ በባልዋ ልብ ስፍራና ቦታ እንዳላት ስለሚያሳያት ለባልዋና ለትዳርዋ ያላትን ስሜት ከምንም ነገር በላይ ከፍ ያደርገዋል።





የሚስቶች ልብ በየጊዜው የማገዶ እንጨት እንደ ሚያስፈልገው እሳት ነው። ያለ ማገዶ እንጨት እሳት እን ደማይነድ ሁሉ የሚስቶች የፍቅር እሳት እንዲነድ የማገዶው እንጨት ሳያልቅ በፊት መጨመር አስፈላጊ ነው። ትናንት በተደረገው ነገር ብቻ ረክተው አይቀመጡም። በየጊዜው መወደድ ፣ መፈቀርና መታሰብን ይፈልጋሉ። ያ የፍቅር እሳት አንዴ የጠፋ እንደሆን ግን መልሶ ማንደዱ ከባድ ይሆናልና ሳይጠፋ በየጊዜው ማገዶውን መጨመሩ ያዋጣል።

ትዳር ሥራ ነው የምንለው ለዚህ ነው። ያነደዱትን የፍቅር ችቦ እንዳይጠፋ ከብዙ ንፋስ ጠብቆ እስከ ፍጻሜው መሮጥን ይጠይቃል። ሰነፍ ሰው ገንዘብን ብቻ ሳይሆን ሚስቱን ም ያጣል። የሰርግ ቀን ልክ ለአንድ ሥራ እንደ ተቀጠርንበት ቀን እንጂ የደሞዝ ቀን አይደለም። ከደሞዝ በፊት ብዙ ስራና ድካም አለና። ስለዚህ ትዳር ሥራዬ ብሎ ላሰበው ፣ ለተጠንቀቀለትና ለተንከባከበው ብቻ ደሞዙ ታላቅ ነው።

ሁለተኛው አክብሮት ነው። አክብሮት የሚለውን ቃል ትርጉም ጠጋ ብለን ያየን እንደ ሆነ ለአንድ ሰው ዋጋ መስጠት ወይንም ውድ እንደሆነ መቁጠር ነው። ሃዋርያው ጴጥሮስ ደካማ ፍጥረቶች ስለሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል ኑሩ ሲል ሴቶች ከወንዶች ይልቅ በስሜታቸው ውስብስብና ስስ በመሆናቸው ነው ብለናል።

ሴቶች የቱንም ያህል የተማሩና የስለጠኑ ቢሆኑ ውበትና ድካም አንድ ላይ ያሉባቸው የሚወደዱ ግን በጥንቃቄ ሊያዙ የሚገባቸው ናቸው። ልክ አንድ የሚያምር ግን በቀላሉ ተሰባሪ የሆነን እቃ በቤታችን እንደምንጠብቀው ሚስቶችን በዚህ አይነት መልኩ ልናከብራቸውና ልንጠብቃቸው ይገባል።

አክብሮት የሚገባው ለሴቶች ብቻ አይደለም። መጽሃፍ ቅዱስ ስለ ቤተክርስትያን መሪዎች ሲናገር 1ኛ ጢሞ 5፥17 *«በመልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት እጥፍ ክብር ይገባቸዋል።»* ከዚህ ቃል እንደምንረዳው ሽማግሌዎች ከተቀመጡበት ወንበርና በሥራቸው ለሚያሳዩት ትጋት ክብር እንደሚገባቸው ነው። ባልም በቤቱ ላይ ጌታ ካስቀመጠው ወንበርና ለቤቱ በሚያሳየው የአስተዳደር ትጋት ከሚስቱ የሚገባውን ክብር ሊቀበል ይገባዋል።

እንዲሁም ልጆች ወላጆቻቸውን ማክበር እንደሚገባቸው በማቴ 15፥4-6 ሲናገር አባትና እናትህን አክብር ይላል። ያንን የማያደርግ ግን በደንጋይ ተወግሮ ይሙት በማለት ጌታ ምን ያህል እርስ በርስ ስላለን መከባበር ግድ እንደሚለው ያሳያል።

እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብን ልጆች አክብሮትን የሚማሩት ከወላጆች እንደሆነ ነው። እርስ በርስ የሚከባበሩ ወላጆች ሥር ያደጉ ልጆች እርስ በርስም ሆነ ለወላጆች በኋላም ትዳራቸውን የማክበር ችግር አይኖርባቸውም።

በዘጸአት 20፥12 *«አባትና እናትህን አክብር እግዚአብሔር አምላክ በሚሰጥህ ምድር እድሜህ እንዲረዝም።»* አክብሮት እድሜን ያረዝማል። ጌታ ለህዝቡ ሊሰጣቸው ባለው ምድር እን ዲወርሱአት ብቻ ሳይሆን በምድሪቱ ውስጥ የረዘመ እድሜ እን ዲኖራቸው ወላጆችን አክብሩ በማለት ይመክራል።

በኤፌሶን 6፥2 *«መልካም እንዲሆንልህ እድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝምልህ አባትና እናትህን አክብር። እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት።»* ሃዋርያው ጳውሎስ ይህንኑ የዘጸአትን ጥቅስ በመድገም ሰው በህይወት ዘመኑ እድሜው እንዲረዝምና በዘመኑ የአምላኩን





መልካምነትን እንዲያይ አክብሮት ምን ያህል አስፈላጊ እን ደሆን ይናገራል።

አክብሮት የትዳር እድሜን ማርዘሙ ብቻ ሳይሆን እኛ በትዳር ውስጥ ያለንን እድሜ ያረዝመዋል። መጋቡት ብቻ በቂ አይደለም። በጋብቻ ውስጥ መቆየት የረዘመ እድሜን ማግኘትም አስፈላጊ ነው። በዚህ ጉዳይ የጌታ ቃል ግልጽ ነው።

በምሳሌ 22፥4 *«ትህትናና እግዚአብሔርን መፍራት ባለጠግነት ክብር ህይወትም ነው።»* ይህ ጥቅስ ክብርና ባለጠግነት ምን ጫቸውን ሲናገር ትህትናና እግዚ አብሔርን መፍራት ነው ይላል። ነገር ሁሉ ምንጭ አለው። ለመ ከበር ምንጩ በትህትና መኖርና ጌታን መፍራት ነው። ባልም ሆነ ሚስት አክብሮትን ለማግኘት አያን ዳዳቸው አክብረኝ በማለት ሳይሆን እንዱ ለሌላው በትህትና በመኖርና በጌታ ፍርሃት ውስጥ በመሆን ነው።

**አክብሮት የትዳር እድሜን ማርዘሙ ብቻ ሳይሆን እኛ በትዳር ውስጥ ያለንን እድሜ ያረዝመዋል።**

ባልና ሚስት መከባበራቸውን በብዙ መንገድ መግለጽ ይችላሉ። እንዱ በየቀኑ በሚናገሩት ቃል እንዱ ሌላውን ማክበሩን ማሳየት ይችላል። ይህንን ስል በማይግባቡበት ጊዜ እንኳን የተመረጡ ቃላቶችን በመምረጥ መናገርንም ጭምር ነው።

በትዳራችን ውስጥ እግዚአብሔርን ከማመስገንበት ነገር እንዱ ባለቤቴም ሆነች እኔ የቱንም ያህል ብንናደድ ወይንም ብንቆጣ አንድም ቀን የስድብን ወይንም የማይገባ ቃል ከአፉ

ችን ወጥቶ አያውቅም። ይህ ለትዳር ፍጹም ጤናን የሚሰጥ መጽሃፍ ቅዱሳዊ መመሪያ ነው።

## 4. አለማወዳደር

**(በትዳር ባልንጀራችን ፊት ሌላን ሰው አለማድነቅ)**

በብዙ ትዳር ውስጥ ካሉት ችግሮች መካከል አንዱ ትዳራችንን ከሌላው ትዳር ጋር ማወዳደር ነው። ሰው እንደ ቤቱ እንጂ እንደ ጎረቤቱ አይኖርም እንዲሉ የእያንዳንዱ ቤት ሥርዓትና ደንብ ኑሮና ህይወት አንዱ ከሌላው ፈጽሞ የተለያየ ነው።

ጌታ በቤተሰቡ ላይ እንዳለው አለማና አቅድ ፣ ጌታን እን ደመታዘባቸውና በህይወታቸው ቅድሚያ እንደሚሰጡት ነገር የአንዱ ቤት ከሌላው የተለያየ ነው። ስለዚህ የሌላውን ሰው ቤት ትዳር ከትዳራችን ጋር እናትን ከሚስት ጋር አባትን ከባል ጋር ማወዳደር የማይገባና ለትዳሩ ትልቅ እንቅፋት ነው።

ለምሳሌ አንድ ባል ጓደኛው ቤት በድንገት እንደራበው ይሄዳል እንበል። ያን ቀን ስለራበው ጓደኛው ቤት የበላው ምግብ በጣም ጣፍጦት ሊመጣ ለሚስቱ እንዲህ ይለታል። መቼም ዛሬ የበላሁት ምግብ እጅ ያስቆረጥማል። የጓደኛዬ ሚስት እንዴት ባለሞያ መሰለችሽ ብሎ በቅን ልብ ግን ባለማ ስተዋል ያወራል።

ሚስትየው ይህንን ሪፖርት ስትተረጉመው ለስዋ እንዲህ ማለት ነው። አንቺ እስከ ዛሬ ድረስ ያበላሺኝ ምግብ ሁሉ የማይረባና የማይጣፍጥ ነው። አንቺ ሞያ የሌለሽ ሴት ነሽ። ካንቺ ይልቅ እስዋ ትሻለለች በሚለው ነው። ይህ ለሚስቱ ትልቅ የስድብና የውርደት ቃል ነው።





ይህ ብቻ አይደለም የሌሎችን ሰዎች አለባበስ አሰራር አመለካከትና አስተሳሰብ ሁሉ በምንም መልኩ ከሚስት ወይንም ከባል ይልቅ አድንቆ መናገር በትዳሩ ላይ የማይጠፋ እሳት እንደመጫር ነው።

## 5. አለመደባበቅ

ለመሆኑ ባል ከሚስቱ ሚስት ከባልዋ የሚደብቁት ነገር ሊኖር ይገባል ወይ? ይህ ባለ ትዳሮች ሁሉ ሊጠይቁት ሊወያዩበት የሚገባ ጥያቄ ነው። የጋብቻ ትምህርት በማስተ ምርበት ጊዜ አንዱ ተጋቢዎችን የምጠይቀው ጥያቄ ይሄ ነው። ባልሽ ሁሉንም ነገር እንዲነግርሽ ትፈልጊያለሽ ወይ? ሚስትህ ሁሉን ነገር እንድትነግርህ ትፈልጋለህ ወይ?።

የሚገርመው መልሱ እንደየሰዉ የተለያየ መሆኑ ነው። አንዳንዶቹ በተለይ ሴቶቹ ቆጣ በማለት ፈጽሞ ምንም ነገር እን ዲደብቀኝ አልፈልግም ሲሉ ሌሎች ደግሞ ባሌ ከሆነ እምነ ዋለሁ ሊነግረኝ የሚገባውን ነገር ብቻ ለይቶ እንዲነግረኝ ነው የምፈልገው ይላሉ።

ሌሎች ደግሞ ምንም ነገር እንዲደብቀኝ አልፈልግም ነገር ግን የሚነግረኝ ነገር በጊዜው ልሰማው የማይገባ ከሆነ ምንም ይሁን ምን በጊዜው ግን እንዲነግረኝ እፈልጋለሁ ይላሉ።

የቱ ነው ትክክሉ? እንባቢ ሆይ የእኔን አስተያየት ከመስ ማትዎ በፊት እስቲ ለጥቂት ደቂቃ ከጽሁፉ ላይ አይንዎን ያን ሱና ለዚህ ጥያቄ በራስዎ መልስ ለመስጠት ይሞክሩ። የእኔን መልስ ከመስጠቴ በፊት ሌላ ጥያቄ ላንሳና ልጠይቅዎ። ለመሆኑ በትዳርዎ ውስጥ ደስተኛ መሆን ነው የሚፈልጉት ወይስ ትክክል?

መቼም አንድ የማይካድ ነገር አለ። ትዳር የጋራና ሁሉን ነገር ተመካክረን የምንኖረው ህይወት መሆኑ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ትክክለኛው መልስ ይሄ ነው ብሎ መደምደም አስቸጋሪ ቢሆንም ሊካዱ የማይችሉ እውነቶችን ግን ማስቀመጥ እፈልጋለሁ።

በመሰረቱ ባልና ሚስት አንድ እንደመሆናቸው መጠን አንዱ ካንዱ የሚደብቀው ነገር ሊኖር ፈጽሞ አይገባም። ባለማወቅ በግድ የለሽነት ወይንም በተለያየ አጥጋቢ ባልሆነ ምክንያት መደባበቅ ሲጀምሩ ግን ትዳሩን መጉዳት ማቁሰል ብሎም መለያየት ደረጃ ሊያደርሱት ይችላሉ። እነዚህ ባል ከሚስት ሚስት ከባል ሊደብቁ የማይገባቸውን ነገሮች በዋነኛነት የሚጠቀሱትን ብቻ በጥቂቱ እንስተን እንያቸው።

1ኛ ገንዘባችንን ወይንም ገቢያችንን ልንደባበቅ ፈጽሞ አይገባም። በትዳር ውስጥ የተጋቡት ባልና ሚስቱ ብቻ ሳይሆን ገንዘባቸውና ንብረታቸው ሁሉ ነው። ትዳር በባልና ሚስት መካከል ያለ ፍጹም የሆነ ውህደት ነው። ውህደቱም በሁሉም ነገር ሊሆን ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነው ይለዋል። ይህን ሲል ገንዘብ በራሱ ክፉ ሆኖ ሳይሆን ሰዎችን ለክፋት የማነሳሳት አቅሙ ትልቅ መሆኑን ለማሳየት ነው። ገንዘብ የምንጠቀምበት የህይወት መሳሪያ እንጂ የህልውናችን ምንጭ አይደለም።

በትዳር ውስጥ ትክክለኛው የገንዘብ አጠቃቀም ይሄ ነው ብሎ ህግ ማውጣት ባይቻልም ባልና ሚስት የሚያገኙት የሁለቱም የገንዘብም ሆነ የንብረት ገቢ በትክክል አንዱ ከአንዱ ሳይደበቅ በሁለቱም መታወቅ ይኖርበታል። የሁለቱንም ገቢ በአንድ ላይ አስቀምጦ ወጪያቸውንም በጋራ ተሳስበው ማውጣት ተቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል። በአፈጻጸሙ ላይ





ግን የሥራ ክፍፍል አድርገው መስራታቸው ይበጅ ይሆናል እንጂ አይከፋም።

በአንዳንድ ቤተሰብ ውስጥ የገንዘብ አያያዝ ችሎታ ያላት ሴት ልትሆን ትችላለች በሌላው ቤት ደግሞ ወንድ ሊሆን ይችላል። ቹኩን ማን ይጻፈው? አዳውን ማን ይክፈለው? እስከተስማሙ ድረስ ይህ ችግር ሊሆን አይገባም። ችግሩ ሚስት ያለ ባል ፈቃድ ወይንም ባል ያለ ሚስት ፈቃድ ሳይስማሙ ወይንም ሳያውቁ በመደበቅ ቤተሰብን ወይንም ጓደኛን ቢረዱ ነው። ይህ አለመተማመንን ከማምጣቱም በላይ ያላቸውን የትዳር ግንኙነት ሊጎዳ ይችላል።

ሌሎች ሰዎችንም ሆነ ቤተሰብን በገንዘባችን መርዳት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ክርስትያናዊ ግዴታችን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቤተሰቡ የማያስብ እርሱ ሃይማኖትን የካደ ሰው እንደሆነ ይናገራል። ይሁን እንጂ የሚረዳው ክፍል የሚረዳው በባለትዳሮቹ ፈቃድ ላይ በተመሰረተ ስምምነት ብቻ ሊሆን ይገባል። የሁሉ ሰው ቤተሰብ አኗኗር አንድ አይደለም። የአንዱ ቤተሰብ በችግር ላይ ያለ ከሆነ ችግር የሌለው ቤተሰብ ክፍል የሆነው ያ ለቀዘቀዘ ሊረዳ የሚገባውን ቤተሰብ መርዳቱ ተገቢ ነው።

2ኛ - የትዳር ጓደኛ ሳያውቅ ወይንም በድብቅ የሚደረጉ ማንኛውም አይነት ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚደረግ ወዳጅነት በትዳር ውስጥ ያለ ሌላው ችግር ነው። በመሰረቱ ባልና ሚስት የትዳር ጓደኝነት ብቻ ሳይሆን የህይወት ጓደኝነትም ሊኖራቸው ይገባል። ከዚህ ባሻገር ከሌሎች ሰዎች ጋር ህብረት ማድረግ ቢቻልም ከማንም ሰው ጋር በድብቅ የሚደረግ ወዳጅነት ግን ሳይታወቅ ትዳሩን እንደ ምስጥ በልቶ ይጥላል። ቢቻል ወዳጅነቱን አብሮ ማድረግ ፤ ካልሆነ ግን የወዳጆችንን ማንነትም ሆነ የምናሳልፍበትን ቦታ በማስታወቅ ማድረግ ይገባል።

በጽሁፌ መጀመሪያ ስለ ሦስቱ የጋብቻ አይነት ሳነሳ አን ደኛው አይነት ፍጹም ያልሆነ ነገር ግን ወደ ፍጹምና የሚያድግ ጋብቻ እንደሆነና ይህም አይነት ጋብቻ አሁን ያለን በት ዘመን ውስጥ ያለ ጋብቻ እንደሆነ አይተን ነበር።

በዚህ አይነት ጋብቻ ውስጥ እስካለን ድረስ ፍጹምነትን ከትዳር ጓደኛችን ውስጥ ማግኘት የማይቻል ነው። ምርጫው የእኛ ነው ፤ ደስ ብሎን ለመኖር ሁልጊዜ ትክክል ሆኖ መኖር ስለማይቻል ምርጫችን ደስ ብሎን መኖር ሊሆን ይገባል። ደስታ ምርጫ ነው እንጂ አጋጣሚ ወይንም እድል አይደለም።

በትዳሩ መልካም ነገሮች ላይ በማተኮር ደስ ብሎን ከኖርን ያሉብንን ችግሮች ቀስ በቀስ በጸሎትና በጌታ ቃል ማስወገድ ቀላል ይሆናል። ትክክል ያልሆኑ ነገሮች ሁሉ ሊታረሙ የሚገቡ ቢሆኑም ትኩረታችን እነሱ ከሆኑ ግን ስህተቱን ስንጠግን ትዳሩን እንዳናፈርስ ልንጠነቀቅ ይገባል።

በትዳር ውስጥ መደባበቅ የሚያመጣውን ጠንቅ አይተናል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ነገሮች ትዳሩን የሚጠቅም እስከሆነ ድረስና በትዳሩ ላይ የሚያመጣው ችግር እስከሌለ ድረስ ለጊዜው የምንደብቃቸው ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህንም በሦስት ክፍል ከፍለን ማየት እንችላለን።

በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን ትእዛዝ ለመፈጸም ስናስብ ድምጹና ትእዛዙ የመጣው ለእንዱ ብቻ ከሆነ እስከ ጊዜው ድረስ በሚስጢር እንጠብቀዋለን። አብርሃም ይስሃቅን ሊሰዋ ሲሄድ ሳራን አማክሮ ቢሆን ኖሮ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያስቸግርም። ይሁን እንጂ ከሞሪያም ተራራ ሲመለሱ ታሪኩን ለሳራ ሳያጫውቱአት አን ዳልቀሩም መገመት ቀላል ነው።





ሁለተኛ እንደ መጋቢ ወይንም እንደ አገልጋይ አንዳንድ ሰዎች የህይወታቸውን ሚስጢር መጥተው ሲነግሩኝ የመጀመሪያ ጥያቄዬ ይህንን ጉዳይ ለባለቤቴ ብነግራት ምን ይመስላችኋል ነው። እንድናገር ከፈቀዱልኝ መንገሩ ቀላል ነው። ካልፈቀዱልኝ ግን መጽሐፍ ቅዱስ የቤተክርስትያንን ሚስጢር ስለ መጠበቅ ስለሚናገር ይህ ሚስጢር ከእኔ ጋር ወደ መቃብር አብሮ የሚወርድ ሊሆን ይገባል እንጂ ለሚስቴ ስላልነገርኩ ትዳሬ ይፈርሳል ብዬ ፈጽሞ ላስብ አይገባኝም። ባለቤቴም በዚህ ጉዳይ ልትጠይቀኝ ፈጽሞ አይገባትም።

በሦስተኛ ደረጃ ባለቤቴ ከሴትነትዋ የተነሳ ልትሸከመው የማትችላቸውን ነገሮች በመንገር እስዋን ከባድ ሸክም አሸክሜ በትዳሬ ላይ ወይንም በቤቴ ላይ ችግር ማምጣት የለብኝም። ማንም ሰው ሊሸከመው ከሚችለው ባላይ የሆነን ነገር መነገር አለበት ብዬ አላምንም።

ለምሳሌ በማገለግልበት ጊዜ እንደ መጋቢ ከባድ ወይንም አስቸጋሪ የሆኑ ለሰው የማይገቡ እንዳንዴ ለጊዜው ለኔም የማይገቡኝ ችግሮች ውስጥ አልፋለሁ። ይሁን እንጂ የማል ፍበት ችግር ከባድ መሆኑን በመግለጽ እንድትጸልይልኝ እነግራታለሁ እንጂ ችግሩ ይህ ነው በማለት ላስቃያት አይገባም። እኔ ለቦታው የሚሆን ጸጋና ሃይል ተሰጥቶኛል እስዋ ግን ሚስቴ ብቻ በመሆንዋ የማትችለውን ሸክም ማሸከም ለትዳሩም ሆነ ለእርስዋ ትልቅ እንቅፋት ይሆናል።

ሚስጥርን ከትዳር ጓደኛው መጠበቅ አላማው መደበቅ አይደለም ፤ ነገር ግን ለትዳሩ የሚጠቅመውን በመለየት ትዳሩን ማቆየት መቻል ነው። መንገር ያልፈለግነውን ነገር መንገር የማንፈልገው ሃጢአትን ለማድረግና ትዳሩን የሚጎዳ ነገር ለማድረግ ሳይሆን ደስተኛ ሆነን ለመኖር ጌታን አክብረን እን

ድንኖር የሚያስችሉንን ነገሮች እንደ በሳል ሰዎች ለይቶ ለማድረግ እንድንችል ብቻ ነው።

በምእራቡ አለም እንዲህ ይላሉ "ጠንካራ ትዳር መያዝ ማለት ለመቆጣጠር የምንፈልገውን ነገር ሁሉ መልቀቅ ማለት ነው።

## 6. የሌሎች ሰዎችን ጣልቃ ገብነትን ማስወገድ

ዘፍጥረት 2፥24 *ሰው አባትና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል*። ኤፌሶን 6፥31 *ሰው አባትና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ*። በእነዚህ ሁለት ጥቅሶችም ሆነ ጌታ እየሱስ ራሱ ይህንን ሃሳብ ጠቅሶ በተናገረበት በማቴዎስ 19፥5 ላይ ይተዋል በማለት በአ ንድ ቃል ብቻ ሲናገር እንድ የመሆናቸውን ሃሳብ ግን በአማርኛ ውም ሆነ በእንግሊዘኛው የተለያዩ ትርጉሞች ላይ ይጣበቃል ይተባበራል በማለት ይናገራል።

ይህ ይተባበራል ወይንም ይጣበቃል የሚለውን ቃል የግሪኩ ትርጉም ተከታትሎ መያዝ የሚል ሃሳብ አለው። ከዚህ ትርጉም እንደምንረዳው የመጣበቁ ጉዳይ የአንድ ቀን ጉዳይ እንዳልሆነ ሲያሳይ የመለየቱ ግን የአንድ ቀን ጉዳይ ነው። መተው ከሆነ ቁርጥ አድርጎ መተውን ይጠይቃል። ቃሉ በግሪኩ መለየትን ወይንም ጥሎ መሄድ የሚለውን ትርጉም ይሰጣል። መለየትን ወይንም ጥሎ መሄድ የሚለው ቃል ትርጉም ስናይ ደግሞ እንደኛ በፈቃድ መተው ወይንም መካድ ማለትን ወይንም በፈቃደኝነት መልቀቅ የሚለውን ትርጉም ያጎላል ።

ሁለተኛው ትርጉም ፈጽሞ ዞር ብሎ አለማየት ማለት ነው። ይህንን ሁሉ ለማለት ያስገደደኝ በርግጥ የጌታ ቃል ሰው እናትና አባቱን ይተዋል ሲል መተዉ ምን ያህል እንደ ሆነ ግልጽ ባለ መልኩ ለማሳየት ነው። ዛሬ የብዙ ባልና ሚስት





ትልቅ ችግር የቤተሰብ ወይንም የወዳጅና ዘመድ ጣልቃ ገብነት ከጌታ ቃል ውጪ መሆኑን ባለመገንዘብ ነው። ቃሉ ተው ካለ መተው ግድ ነው።

መተው ስንል ሙሉ ለሙሉ ከዚህ በኋላ የራሳቸውን ኑሮ ለመኖር በራሳቸው አመራር በራሳቸው እውቀትና በራሳቸው እምነት ባልና ሚስት ብቻ ተስማምተው መወሰን ይገባቸዋል እንጂ በማንም ጣልቃ ገብነት ይህንን አዲስ ህይወት ሊመሩት አይገባም ነው።

ይህንን ስንል ቤተሰብ በጋብቻ ውስጥ ምንም አያገባውም ማለታችን አይደለም። የቤተሰብ ድርሻ እንዳለ የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ ቤተሰብ መወሰንና እንዱን ብቻ ወገን በመያዝ ትዳሩ መካከል ገብተው መከፋፈል ፈጽሞ ከጌታ አይደለም።

ቤተሰብ ለጋብቻ በሰጡአችው ባለትዳሮች መካከል የውሳኔ ጣልቃ ገብነት ባይኖራቸውም የመምከር ፣ መንገድ የማሳየትና የመርዳት ሃላፊነት አለባቸው። እዚህ ላይ ነው የወላጆች ጥን ቃቄ የሚያስፈልገው። በምእራቡ አለም ልጃቸው የሰጡትን ሰው የህግ ልጄ ብለው ሲጠሩ እኛ አማት ምራት በማለት ልዩነትን የሚፈጥር ቃል እንጠራለን። ይህን ስል የራሴን ባህል ለማቃለል ሳይሆን እነርሱ የሰጡት ስም የሚያቀራርብና በቤተሰብ መካከል ልዩነት እንዳይኖር የሚረዳ መሆኑን ለማሳየት ብቻ ነው።

ከስሙ እንደምንረዳው የህግ ልጅ ናቸው እንጂ የውጪ እንግዳ ወይንም ልዩ ሰው አይደሉም። ወላጆች ልጃቸውን ከዳሩ በኋላ የተቀበሉትን ሰው ልክ እንደ ልጃቸው አድርገው መያዝ ማስብ መምከር ይኖርባቸዋል። ይህንን ቢያደርጉ ለትዳሩ የሚያስፈልግ ጠቃሚ ምክር ካላቸው ለይተው ልጃቸውን ብቻ ከመምከር ይልቅ ሁለቱም ልጆች ናቸውና አብሮ መምከር ፣ ማስተማርና መምራት ይቻላል። ይህም

ተጋቢዎቹ በሃሳቡና በምክሩ እስከተስማሙ ድረስ ብቻ እንጂ አሰገድዶ ወላጅ ስለሆኑ ብቻ ምንም ነገር ማሰወሰን ተገቢ አይሆንም።

እንግዲህ ይህ እንዲሆን የተጋቢዎች አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ለመጠቆም እወዳለሁ። የትኛውም ወላጅ አንዱን ብቻ በመለየት ለመምከር ሲሞክር አደጋውን በማየት ልጅ ወላጅ ቢቆጣም ቢያዝንም በዚህ ምክር ውስጥ ባለቤቱ ከሌላ ወይንም ከሌሎች ምንም አይነት ምክር አልቀበልም የማለት መብታቸውን ማስከበር ይገባቸዋል። ይህንን ቢያደርጉ አንደኛ ራሳቸውን ይጠብቃሉ ሁለተኛ ወላጆችም ለትዳር ጓደኛቸው አክብሮት እን ዲኖራቸው ያደርጋሉ።

ሰም ይወጣል ከቤት ይከተላል ጉረቤት እንዲሉ የትዳር ጓደኛዬ በወላጆቼ ፊት ያላት አክብሮትን የሚወሰነው እኔ በወላጆቼ ፊት ያከበርኳትን ያህል ብቻ ነው። በማንኛውም ውሳኔ ውስጥ ያለ ባለቤቴ እንደማልወሰን ብቻ ሳይሆን ምክ ሩንም ያለ ባለቤቱ አልሰማም ካልኩ የወላጆቼ ምክር በርግጥ ከልብ የሆነና የሚጠቅም ሊሆን ይችላል። ወላጆች ግን አይ መምከር የምፈልገው ብቻህን ወይንም ብቻሽን ነው ካሉ ከጀርባው ሳይታወቅ ቤትን የሚያፈርስ ነገር አለውና ልንጠነቀቅ ይገባል።

ይህንን በወላጆች ላይ ብቻ በማተኮር ተናገርኩ እንጂ የቅርብ ዘመድ ጓደኛ በትዳሩ ላይ ጣልቃ ለመግባት ከሞከሩ እንዚ የማለትና ቤቱን ከመፍረስ የመጠበቅ ሃላፊነት የባ ለትዳሮች ነው።

## 7. የትዳር ባልንጀራችንን ፍላጎት መጠበቅ

ባልና ሚስት አንድ ናቸው ስንል ልዩነታቸውን ለአንድነት ይጠቀሙበታል ማለታችን እንጂ የተለያየ ስጦታና ፍላጎት





የላቸውም ማለታችን እንዳልሆነ አይተናል። ብዙ ጊዜ የእ ነዚህን ሁለት ነገሮች ማለት አንድነታችንንና ልዩነታችንን በሚገባ ለይተን መቼ የቱን እንደምንጠቀም ካለማወቅ የተነሳ ቤተሰቡ አንዱ በአንዱ ልዩ ስጦታ ሊያገኝ የሚችለውን በረከትና ጥቅም እናስቀራለን።

በዚህኛው ነጥብ ላይ ላተኩር የምፈልገው እያንዳንዱ ሰው ከጌታ የተሰጠው ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ እንዳለው ለማሳየት ፣ ከዚህም ጋር በህይወት ውስጥ የተለያየ ፍላጎት እን ዳለና ይህንንም እንዴት ለቤተሰቡ ጥቅም መጠቀም እንደምን ችል ነው።

እኔና ባለቤቴ እንደተጋባን ከገጠሙን ችግሮች መካከል አንዱ የዚህ አይነቱ ነበር። እኔ በማሪና የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋች እንደመሆኔ መጠን አንድ ጊዜ የሙዚቃ መሳሪያ ይዤ ከተቀመጥኩ ለሰአታት እስዋ መኖርዋን ሁሉ አስክረሳ ድረስ እጫወታለሁ አጠናለሁ መዝሙሮችንም ለመጻፍ እን ሳለሁ።

በዚህ ጊዜ ባለቤቴ አብሪያት እንድሆን ብትጠቅሰኝ ብትጠራኝ ብትጎተጉተኝ የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ ብዬ ስራዬን አቀጥላለሁ። ችግሬ ተነሰቼ ከሄድኩ የገባሁበትን የሙዚቃ መን ፈስ ለማጣት መገደዴ ነው። አልነሳም ካልኩ ደግሞ ከባለቤቴ ጋር ችግር ልፈጥር ነው። መንፈሱን ከማጣ እሰዋን አሰረዳለሁ በማለት ሳላውቀው እሰዋን መጉዳት ጀመርኩ።

በዚህ መካከል የሚነሱት ችግሮች ከእለት ወደ እለት እየጨመሩ ሲመጡ የቤቱን ሰላም ለመጠበቅ ሰል ሳላውቀው የነበረኝን ፍላጎት ማጣት ጀመርኩ። ከዚሁ ጋር የቤተሰብ ሃላፊነት የአገልግሎት ብዛትና የተለያዩ የሁብረተሰብ ጫናዎች

ሲበዙ በውስጤ በህይወቴ ዘመን ሁሉ ከሚያረካኝ ነገር እየራቅሁ መጣሁ።

ይህ የእኔ ታሪክ ብቻ አይመስለኝም። ብዙ ባለትዳሮች ከመጋባታቸው በፊት የነበራቸውን ህልምና በህይወት ውስጥ ሊያደርጉት ያሰቡትን ቁም ነገር ልክ እንዳገቡ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ሲጥሉት ይታያሉ። አንድም ከባለቤታቸው ጋር ጊዜ አብሮ ለማሳለፍ በሚደረገው የቤተሰብ ግዴታ ሲሆን አልያም ያላቸውን ጊዜ በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል እውቀት ከማጣት የተነሳ ይሆናል።

ከጥቂት አመታት በፊት አንዲት የቤት እመቤት በባልዋ ገቢ ብቻ የምትደዳደር የነበረች አሜሪካዊ የልጆች እናት የሆነች ሴት ስለ ስራችው ሥራ በቴሌቪዥን ላይ ታሪኳ ሲነገር ሰማሁ። ይህች እናት በውስጥዋ በኮንፒተር አለም ውስጥ አንድ አዲስ ግኝት አመጣለሁ የሚል ህልም ነበራት።

ይሁን እንጂ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ጊዜና የተመቻቸ ሁኔታ ስላልነበረት በቤትዋ ውስጥ በቀን ከእንቅልፍዋ ጊዜ በመስዋትና የእረፍት ጊዜዋን ሁሉ በዚሁ አላማ ላይ ለአ ሥር አመት ካሳለፈች በኋላ አንድ አዲስ ነገር አገኘች። በዚሀ ምክንያት ያንን ሃሳብ በመሸጥ በሚሊየን የሚቆጠር ገንዘብ አገኘች። ይህም የእርስዋንና የቤተሰብዋን ኑሮ ለመለወጥ ምክን ያት ነበር። ከገንዘቡም ባሻገር በህይወት ላይ አንድ ቁም ነገር ሰርቶ ማለፍዋ ምን ያህል እንዳረካት ትናገር ነበር።

ለመሆኑ ትዳር በህይወት ላይ ያለንን ህልም ወይንም ልን ሰራው ያለንን ቁም ነገር የሚገድል ቦታ ነውን? ምንም እንኳን ይህ በብዙ ሰዎች ህይወት ላይ እውታነት ያለው ቢሆንም ትክክለኛ ትዳር ግን አንዱ የሌላውን ስጦታና ስራ በመደገፍ የተሻለ ሰው እንዲ ሆን የሚረዳበት ቦታ እንጂ በውስጡ





ያለውን ህልም መግደያ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ከአንድ ሰው ይልቅ ሁለት ይሻላል ሲል ሁለት መሆናቸው ለሰራው አፋጣኝነትንና ቅልጥፍናን ሊሰጥ ይገባዋል እንጂ የህይወትን ህልም ማደብዘዝ አይገባውም።

የኔ ወንድም በሚስትህ ውስጥ ያለ ተፈጥሮአዊ ስጦታ ምንድን ነው? ያንን ለማውጣት የማበረታታት የመርዳት ሃላ ፊነት አለብህ። የኔ እህት የባልሽ ተፈጥሮአዊ ስጦታ ምንድን ነው? ያንን ለማውጣት የመርዳት የማበረታታት ሃላፊነት የአንቺ ነው። በህይወት ውስጥ የተሻለ ሰው እንዲሆን ለቁም ነገር ሥራ ሰርቶ እንዲያልፍ ማገዝ የአንድ አስተዋይ ባለ ትዳር ትልቁ ስራ ነው።

በትዳር ውስጥ ትልቅ ስራ ሰርቶ ማለፍ ያስመካል እንጂ ከአመት አመት እርስ በእርስ ተፋጦ ወይ ለራስ ያልሆነ ወይ ለሌላው ያልሆነ ህይወት ኖሮ ማለፍ ከአንድ ክርስትያን የሚጠበቅ የህይወት አደራ አይደለም። ሥራ ክቡር ነው በየት ኛውም አለም የትኛውንም ስራ እንሰራ ግን በሥራችን ለውጥ አምጥተን ፍሬ አሳይተን የራሳችንንና የህብረተሰብን ኑሮ ከሁሉም በላይ በአምላካችን መንግስት ላይ ፈቃዱን ፈጽመን ማለፍ ይጠበቅብናል ።

ይህ ችግር በብዙ ከሌላው ህብረተሰብ ይልቅ በእኛ ህብረተሰብ ውስጥ ጎልቶ ይታያል። በእኔ ግምትና አስተያየት ሁለት ትላልቅ ችግሮች አሉን። አንዱ በፕላን (Planning) አለ መኖር ሲሆን ሁለተኛው የሰአት አስተዳደርን (Time Managmenet) አለማወቅ ነው።

ስለእነዚሀ ሁለት ነገሮች በጥልቀት ለመጻፍ አላማዬ ባይሆንም አንዳንድ ሃሳቦችን ልጠቁም። በመጀመሪያ በእቅድ ስለ መኖር እንነጋገር። በምሳሌ 16፥1-3 «*የልብ አቅድ የሰው*

*ነው። የአንደበት መልስ ግን ከእግዚአብሔር ነው። ለሰው መን ገዱ ሁሉ ንጹህ መስሎ ይታየዋል መንፈሻ ሃሳቡ ግን በእግዚ አብሔር ይመዘናል። የምታደርገውን ሁሉ ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ አቅድህም ሁሉ ይሳካልሃል።»*

የልብ አቅድ ከሰው ነው። የአንደበት መልስ ግን ከእግዚ አብሔር ነው ሲል በህይወታችን ላይ ለሚሆኑት ነገሮች ሁሉ የማቀድ ሥራና ሃላፊነት የሰው እንደሆነ በግልጽ ተቀምጦአል። ጌታ መልስ የሚሰጠው እኛ ላቀድነው ነገር ብቻ ነው። እኔ ማቀድ ሲያቅተኝ የእኔን ህይወት ሌሎች ሰዎች ወይንም ሌሎች ነገሮች ባቀዱልኝ መሄድና መኖር ግድ ይሆናል።

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሰጠው ትልቅ ሃብት መካከል ፈቃድንና የፈቀደውን ነገር ለማግኘት መንገዱንና ጊዜውን የማመቻቸቱን ሥራ መስጠቱ ነው። ሰው መሆን ፈልጎ መሆን የማይችለው ነገር የለም ይባላል። ይህ ማለት ሰው ለመሆን የፈለገውን ነገር አቅዶ ጊዜ አስከሰጠው ድረስ ሊሆን የማይችለው ነገር የለም ለማለት ነው።

በትዳራችን ውስጥ ስለ ትዳራችን ስለ ልጆቻችን ስለ ገን ዘባችን ስለ የወደፊት የአጭርና የረጅም ጊዜ አቅድ ማውጣት ማለት የወደፊት ኑሮአችንን ከወዲሁ እንደ መጻፍ ይቆ ጠራል። ጌታ ራሱ በቃሉ ደግፎ የልብ አቅድ የሰው ነው ብሎናል። ያቀድነው ከሌለ ከጌታ ዘንድ መልስ የለም። ጌታ በማንም ህይወት ላይ ተአምርን ይሰራል የሚሰራው ተአምር ግን በሰውየው ልብ ውስጥ የታሰበንና የታቀደውን ነገር ነው።

በቤተሰቦች መካከል ጌታ አድልዎ አላደረገም። ልዩነቱ አንዱ ያቅዳል ሌላው አያቅድም ። በቤተክርስትያናችን ውስጥ አንድ ባልና ሚስት በመካከላቸው ያለመግባባት ተፈጥሮ ለምክር እኔ ቢሮ መጡ። እነዚህ ባለትዳሮች የሚዋደዱ ጌታን





የሚፈሩና የሚያገለግሉ ናቸው። የነበራቸው ችግር አንዱ የገን ዘብ ችግር ነበር። ይህንን ችግር በሰማሁ ጊዜ ከጸሎት ባሻገር የመከርኳቸው እንዲያቅዱ ነበር።

በገንዘብ አኳያ ያላቸውን ችግር ለመፍታት አቅዳቸው ይህንን ይመስላል። አስቀድሞ ባልየው የሚፈልገውን የትም ህርት አይነት እንዲማር ሚስት ደግሞ ሁለት ስራ እየሰራች እሱ እንዲማር እንድታደርግና ልክ እሱ ትምህርቱን እንደጨረሰ በተራው እስዋን እንዲያስተምር ነበር። ይህ አቅድ በጊዜ ሲወሰን ከአራት እስከ አምስት አመት እንደሚወሰድ ተገ መተ።

ይህንንም አቅድ ለጌታ አሳልፈን ሰጠን ጌታም ይህንን አቅድ አየ። ልክ እንደታቀደው እንዳቸው ሌላውን ለማስተማር ሁለቱም ዋጋ ከፈሉ። ባልየው ሚስቱን ሲያስተምር ትምርትዋ ፋታ የማይሰጥ ስለነበረ ከቤት ጽዳት እንስቶ ምግብ ስርቶ በማብሰል አገለገላት። እስዋም እንደዚሁ። ዛሬ እነዚህ ቤተሰቦች ተባርከው ቤታቸውን ማስተዳደር ብቻ ሳይሆን ወደ ተለያየ ቦታ በመሄድ የመገናኛትና ለጌታም ሥራ በገንዘባቸው ትልቅ አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው። ልዩነቱን ያመጣው አቅድ ብቻ ነው። ባያቅዱና በአቅዱ መሰረት ነገሮችን ለማከናወን ባይተጉ ዋጋ ባይከፍሉ ኖሮ ዛሬ ከአምስት አመት በኋም ኑሮአቸው ልክ ከአምስት አመት በፊት እንደነበረው የጭቅጭቅና የችግር ይሆን ነበር።

ወንድሜና እህቴ በቤታችሁ ላለው ማንኛውም ችግር መፍትሄው ጸሎት ብቻ አይደለም። ጸሎት በጣም አስፈላጊና ታላቅ የሆነውን የጌታን እጅ የሚያንቀሳቅስ ቢሆንም ግን ለምን ነገር ነው የምንጸልየው? ያንን በጌታ ፊት ግልጽ አድርጎ ማቅረብ ያስፈልጋል።

የብዙ ሰው ጸሎት ይህንን ይመስላል። ጌታ ሆይ አባክህ ባርከኝ አባክህ አስበኝ አባክህ ከዚህ ችግር አውጣኝ። ጸሎቱ ጥሩ ነው ፤ ጌታ ግን የሚለው ከዚህ ችግር ለመውጣት ምን ያቀድከው ነገር አለ? በምን በኩል ልባርክህ? እንዴት ላስብህ? ነው። አሁንም ቃሉ በምሳሌ 16፥1-3 የሚለው *የልብ አቅድ የሰው ነው። የአንደበት መልስ ግን ከእግዚአብሔር ነው።*

የጊዜ አስተዳደር (Time Managmenet)

ጌታ ኢየሱስ ቀን ሳለ የላከኝን ስራ ልፈጽም የገባኛል ማንም ሊሰራ የማይችልበት ሰአት ይመጣልና በማለት የተሰጠችውን አጭር ጊዜ በአግባቡ በመጠቀም እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ስራ በምድር ፈጽሜ አከበርኩህ በማለት አባቱን ያከበረበት መንገድ አንዱ ጊዜውን በአግባቡ በመጠቀም እን ደነበረ ተናግሮአል። ብዙ ክርስትያኖችም ሆኑ ቤተሰቦች ጊዜአቸውን በአግባቡ በመጠቀም ጌታቸውን ማክበር እን ደሚችሉ አያውቁም።

በዚህም ምክንያት በአልባሌ ነገር የሚባክነው ጊዜ ለጌታ ቸው ሊያመጡት የሚችሉትን ክብር ከመቀነሱ ባሻገር ደስተኞች ሆነው እንዳይኖሩ አድርጎአቸዋል። ዛሬ የምትኖሩት ኑሮ ዛሬ የምሰሩት ሥራ ውጤቱ ለረጅም ዘመን ጊዜአችሁን በምን ላይ እንዳዋላችሁ የሚጠቁም ነው። ጊዜዬን ያልሰጠሁት የኔ የሆነ ነገር የለም።

ንጉሥ ሰለሞን እግዚአብሔር የሰራቸውንና የሚሰራቸውን ነገሮች ሁሉ በጊዜአቸው ብቻ እንደሆነ ሲገልጽ ሁሉን በጊዜው ውብ አደረከው በማለት ተናግሮአል። ይህ ክፍል እንደ ሚያስረዳን የነገር ውበት ያለው በራሱ በነገሩ ብቻ ሳይሆን የሚደረገው ነገር በጊዜው መደረጉ እንደሆነ በግልጽ ያሳያል።





ብዙ ሰዎች የሚያደርጉትን ነገር የሚያደርጉት በጊዜው አይደለም። ይህም ነገሮችን በጊዜው በማድረግ ያለውን ጠቀሜታ ቸል ስለሚባል ነው። በአገራችንም ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ። ላለፈ ክረምት ቤት አይሰራለትም። በማለት በጊዜው ነገርን ማድረግ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ተርተዋል።

እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ሳያዳላ በእኩል ደረጃ ሃያ አራት ሰአት ሰጥቶአል። ልዩነቱ በዚህ በሃያ አራት ሰአት ውስጥ ምን አደረግንበት ነው። ጊዜን ማፍጠንም ሆነ ማዘግየት ስለ ማይቻል ጊዜን ማስተዳደር (manage) አይቻልም። ነገር ግን ጊዜን ማስተዳደር (manage) ማለት ራስን ማስተዳደር ማለት ነው። ይህ ማለት በተሰጠን ሃያ አራት ሰአት ውስጥ ምን ማድረግ እንደምንፈልግ አውቀን በአትኩሮ መኖር ማለት ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ስለ ጊዜ አስተዳደር ያሉትን መመሪያዎች መከተል ግድ ነው።

ገበያ ቦታ ሄደን የምንፈልገውን ነገር ገዝተን ሳንጨርስ ገንዘብ አጥሮን ያውቃል? ገንዘብ እንደሚያጥረን ሁሉ ጊዜም ያጥረናል። ገንዘብ ሲያጥረን ገንዘባችንን የት እንዳጠፋነው እን ደምናስብ ሁሉ ጊዜም ካጠረን ጊዜያችንን የት እንዳጠፋነው ማሰብ ይኖርብናል። ወደ ገበያ ቦታ ሲሄድ በምን አይነት ገን ዘብ ምን እንደሚገዛ ያላቀደ ሰው ሲመለስ ያን ሁሉ ገንዘብ ምን አደረኩት? ይላል። ይህ ሰው ገንዘቡን ምን እንዳደረገው ለማወቅ የገዛው ነገር ምን እንደሆነ ተቀምጦ ማሰብ አለበት። ልክ እንደዚሁም ሁሉ ብዙ ሰው የቀኑን ጊዜ ምን ሲያደርግ እንደዋለ ስለማያውቅ ተመሳሳይ ጥያቄ መጠየቁ አይቀርም። ልክ እንደ ጥያቄው ሁሉ መልሱም በቀኑ ውስጥ ምን ሲያደርግ እንደዋለ ተቀምጦ የማያስብ ሰው ገንዘቡን የት እንዳዋለው የማያውቅ ሰው አይነት ይሆናል።

ገንዘባችንን የት እንዳጠፋን ለማወቅ የምንችለው ስን መዘግበው ብቻ እንደሆነ ጊዜአችንንም የት እንዳጠፋን የምና

ውቀው ስንመዘግበው ብቻ ነው። ስለዚህ እንቅስቃሴአችንን የምንመዘግብበት የጊዜ ሰንጠረዥ የግድ ያስፈልገናል። ይህን ማድረግ ለብዙ ሰው እንደ ትልቅ ሥራ ነው። ነገር ግን ራሳችን ን እስገድደን በማስልጠን ይህንን ብናደርግ የጊዜ ባለ ጠጎች እንድንሆን ይረዳናል። ይህም በምንፈልገው ጊዜ የምንፈልገውን ነገር ለማድረግ ያስችለናል።

ጊዜአችንን በትክክል በእቅድ መጠቀም ስንጀምር የቤተሰባችን ህይወት ይለወጣል። ለሁሉ ነገር ጊዜ ይኖረናል። ጌታን ለማምለክ ለመጸለይ የቤተሰብ ጊዜ አብሮ ለማሳለፍ ለመዝናናት። ይህንን ለማድረግ በሳምንቱ ውስጥ እቅደን ጊዜ መፍጠር እንችላለን።

ከዚህ በታች ለብዙ ቤተሰቦች ይረዳ ዘንድ ጊዜን ስን ጠቀም ምን ማድረግ እንዳለብን የሚገልጹ ጥቂት ሃሳቦችን ልጠቁም።

- አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማድረግ በቂ ጊዜ እንዳለ ሁልጊዜ ራስህን ማስታወስ
- የሥራ ቅደም ተከተሎችህን አስቀምጦ ቅድሚያ መስጠት ያለባቸውን በተቻለ ፍጥነት መስራት።
- በእቅዳችን መሰረት በቀን ውስጥ ምን እንዳደረግን ራሳችንን መገምገም።
- ቀናችንን ከባድ ናቸው በምንላቸው ሥራዎች መጀመር አእምሮአችንና ሰውነታችን ሳይደክም ቶሎ ለመጨረስ እንደሚረዳ እውቆ ቀላል ሥራዎችን ወደ ኋላ ማድ ረግ።





- በአስቸኳይና በአስፈላጊ ነገሮች መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ ጊዜአችንን በአግባቡ ለመጠቀም እንደሚረዳ ማወቅ

ብዙ ጊዜ አስቸኳይ የምንላቸው ነገሮች ጠቃሚ አይደ ሉም። ጠቃሚ የምንላቸው ነገሮች ወደ ግባችን የሚወስዱንና ከረጅም ጊዜ በኋላ ዋጋ የሚያስገኙ ናቸው።

## 8. ራስን መጠበቅ

ያለንበት አለም ከምንገዜውም ይልቅ እየተለወጠ መሄዱን ከማናችንም የሚካድ አይደለም። የሰው ልጅ ስልጣኔ በአውቀቱም ሆነ በስራው እንዲሁም በባህሉ ከፍተኛ ለውጥን እያሳየ ነው። እንዳንዱ በመልካም ሌላው በክፉ። ታድያ ይህ ንን የስልጣኔ አካሄድ ያላስተዋለና አስቀድሞ ያልተጠነቀቀ ሰው ሳያውቀው ያ ድንገተኛ ጎርፍ እሱንም ቤቱንም ይዞ ሊሄድ እን ደሚችል ማሰቡ ትልቅ ማስተዋል ነው።

ምንም እንኳ ስልጣኔ ለሰው ልጆች እድገት ያበረከተው አስተዋጽኦ እጅግ ታላቅ ቢሆንም በተለይ የሰውን ልጆች የሞራል ህይወት ከምናስበው በላይ ማበላሸቱ አሌ የሚባል አይደለም። ታድያ ይህ የሞራል ውድቀት ከውጪ ባለው ህብረተሰብ ላይ ብቻ ሳይሆን ቤተክርስትያንንም እያንገዳገዳት ያለ ይመስላል።

እንዳንዱ ነገር የአደባባይ ሚስጥር ሆኖ ስለማይወራ እንጂ ሰው የልቡን ገልጦ ቢናገር ሁሉ ሰው የሚለው ነገር እን ዳለው ግልጽ ነው። እያመራሁ ያለሁት ይህ የሰው ልጆች ስልጣኔ በትዳር ላይ ያመጣውን ጥቃት ለየት ባለ መልኩ ለማሳየት ነው።

በቀደመው ዘመን የነበሩ ወንዶች ከቤታቸው ወጥተው እስኪገቡ በአይናቸው የሚገባ ፈተናም ሆነ ውድድር አንብዛም ነበር። የአሁን ዘመን ግን ባሎችንም ሆነ ሚስቶችን ሳያውቁት ወዳልተፈለገ ውድድር እየሳበ ትዳሩን ሊገነጥል ተነስቶአል።

ዛሬ ከቤት ውስጥ አንድ ባለ ትዳር ወጥቶ ቤቱ እስኪመለስ የሚያያቸው ሴቶች አለባበስ ወይንም በየመንገዱ የሚለጠፉ ፖስተሮችና በመስሪያ ቤቱ በአስፒል ጫማ ፤ አጭር ቀሚስ ፣ ደግሞም ደረትዋንና ጀርባዋን በሚያሳይ ልብስ ፤ በሚያውድ ሽቱ አብሬው የምትሰሬውን ሴት ሲያይ ቆይቶ ወደ ቤቱ ሲገባ ደግሞ ሚስት ወጥ እየሰራች ሽቶ ሽቶ ሳይሆን ወጥ ወጥ እየሸተተች በጥሩ ልብስ ሳይሆን ባረጀ የቤት ልብስ ጸጉርዋ በሻሽ ተጀቡና ልጅ ታቅፋ ያያል።

በዚህ ጊዜ ነው ይህ ነገር ሲደጋገም ሳያውቀው በውጪ የሚያያት ሴት በቤትዋ ስለማያውቃት የውጪውን ብቻ በማየት ሳያውቀው ማወዳደር የሚጀምረው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ለሚስቱ ያለው አመለካከት ተለውጦ ከፍቅር ይልቅ ጥላቻ ከአክብሮት ይልቅ ንቀት ውስጡ እየገባ ቤቱን ችላ ማለት ይጀምራል።

ይህ ችግር እንደ ወንዱም ባይሆን በሴቶችም ላይ ይታያል። ሴትዋም ባልዋ ከቤት ሲነጫነጭ የሚያስፈልጋትን እንክብካቤ ሳይሰጣት ይቀርና ወደ ሥራ ቦታ ስትሄድ ግን በአ ይኑ አተኩሮ የሚያያትን በጥሩ ቃልና በአክብሮት የሚያና ግራትን ስታይ ደግሞም ጺሙን የተላጨ ጸጉሩን በልዩ መልክ ያበጠረ በጥሩ አለባበስ ያሸበረቀውን ስታይ ሳታውቀው ለባልዋ ያላትን አክብሮት በማጣት ልብዋ ከቤትዋ መሸፈት ይጀምራል።

እውነታውን ንቀን በምክርና በውይይት ይህንን የህይወት ውድድር ማሸነፍ አንችልም። ስለዚህም ሚስት በተቻለ መጠን





ባልዋ ከመምጣቱ በፊት የምትሰሬውን የወጥ ሥራ አስቀድማ ጨርሳ እንደ አቅምዋ በሆነ ማለፊያ ልብስ ለብሳ ጸጉርዋን ተሰርታ አምሯ ብትጠብቀው ከውጪ ያለውን ተጽእኖ በብዙ መቀነስ ብሎም ማጥፋት ይቻላል።

ወንዱም ቢሆን በሥራ ቦታ ያሉትን ሴቶች እንደሚያከብር ሚስቱን ቢያከብር በእረፍት ቀኑ ሚስቱ ከውጪ ስትመጣ ጺሙን ተላጭቶ ጸጉሩን አበጥሮ ጥርሱን ተቦርሾ ሻወር ወስዶ ሚስቱን ቢጠብቃት በውጪ ካለ ውድድር ልብዋን ሊጠብቅላት ይችላል።

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ባለትዳሮች ካገቡ በኋላ ህይወት በውጪ እንጂ በቤታቸው ውስጥ የሚኖሩ አስከማይመስሉ ድረስ በቤታቸው ያላቸውን ገጽታ ፈጽሞ ባለመጠንቀቅ በትዳሩ ላይ ትልቅ ጉዳት ያስከትላሉ። ያለንበት ዘፋ አለም ብቻ ሳይሆን ዘፋ ዘመንም እንደሆነ እንርሳ። ሃጢአት ሃጢአት መባሉ ቀርቶ ሌላ የስልጣኔ ስም ስለተሰጠው ሰው ኄታውን መፍራት ትቶ በአለም ውስጥ እንዳለ ሁሉ በክርስትያን ቤተሰብም ውስጥ ያው ሆኖ ይታያል።

የስርጉ ማግስት ያለውን መነፋፈቅና መከባበር ከጸሎትና ከመንፈሳዊው ነገር ባሻገር በኑሮአችንም ብንደግፈው ለትዳራችን ዘለቄታነትን ይሰጣል እንጂ ጉዳት የለውም።

መጽሐፉ ብዙ ጥናትና ምርምር በማድረግ የተጻፈ በመሆኑ ወንድማችን ፓስተር እንድሪያስ ሐዋዝን ከልብ ላመሰግነውና እግዚአብሔር ይባርክህ ለማለት እፈልጋለሁ። ከቅድመ ጋብቻ በፊት ያሉና በጋብቻ ክልል ውስጥ ያሉ መጽሐፉን በማንበብ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ።

*ፓስተር ዳንኤል መኮንን*

መልካም ትዳር እንደ ሎተሪ በእድል ላይ አይመሰረትም። ጥሩ ባል ለማግኘት ጥሩ ሚስት፣ ጥሩ ሚስት ለማግኘት ጥሩ ባል መሆን ይጠይቃል። የጋብቻ ስኬትና ጥሩ ውጤት፣ ባልና ሚስት ለውጤቱ ተግተው በሚያደርጉት ድካም ላይ ይመካል። ሥራ አለው።

የአማኞች ጋብቻ ከሌሎች ልዩ የሚያደርጉት ነገሮች ቀስ በቀስ እየተቀረፉ በመውደቅ ላይ ባሉበት በዚህ ዘመን ወንድማችን ፓስተር እንድሪያስ ሐዋዝ ለወቅቱ የሚገባ ሃሳብ ያዘለች መጽሐፍ አቅርቦልናል።

በዚህች መጽሐፍ ገጾች ፓስተር እንድሪያስ ሐዋዝ ጋብቻ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ዘለቄታ ያለው ቋሚ ቃል ኪዳን መሆኑንም ጭምር በማስረገጥ ትዳርን የጣፈጠ ለማድረግ ምን እንዲያስፈልግ አይታውን በግልጽነት እንድንመለከት አቅርቦልናል። ስለዚህ አንብበን እንጠቀም፤ የተማርነውንም መልሰን ለሌሎች እናስተላልፍ።

*ፓስተር ተስፋ ወርቅነህ*

ሁላችን ትዳር የተቀደሰ የእግዚአብሔርን ስጦታ መሆኑን እናው ቃለን። የማናውቀው ወደ ተቀደሰ ትዳር እንዴት እንደሚገባና እንዴት መቀጠል እንዳለበት ነው። ይህንን በተመለከተ በጣም የምንወደው ወንድማችን ፓስተር እንድሪያስ ሐዋዝ ባለው በእግዚአብሔር ቃል እውቀትና በረጅም ዘመን የትዳር ልምምድ እጅግ ወቅታዊና ጠቃሚ የሆነ መጽሐፍ ጽፎአል።

ፓስተር እንድሪያስ ሐዋዝ ላገቡትም ሆነ ገና ለሚያገቡት የትዳርን ጽንስ ሃሳብ በመተንተን ያቀረበውን ትምህርት ከመጽሐፉ ያነበብኩት በመገረምና በመደነቅ ነው። እርስዎም ስለ ትዳር የሚያነሱት ጥያቄ ካለ ወይም የሚያቀርቡት ምስጋና ፥ ይህ ምርጫ የሌለው መጽሐፍ ነው። ፓስተርን ጌታ ይባርከው።

USA $10.00
CANADA $12.00

*ቄስ/ዶክተር ቶሎሳ ጉዲና*

Litho Printing • Houston, TX